ቀሲስ ኃይሉ

ያለ ፡ መምህር ፡ አስተማሪ ።

ከአለቃ ፡ ጽጌ ፡ ገብረ ፡ ኪዳን

ለማስተማሪያ ፡ ተሰናዳ ።

የመጽሐፉ ይዞታ ፤

፩ኛ ፡ የጎብርና የሰም ፡ ለበስ ፡ ቅኔዎች ሁኔታና መደበኛ አፈታት ።

፪ኛ ፡ ቀላል የጎብር ቅኔ አፈታት ።

፫ኛ ፡ የጎብር ቃሎችና አፈታታቸው ።

፬ኛ ፡ የፊደላት ወይም የቃላት ቅኔ አፈታት ።

፭ኛ ፡ የቅኔ ሐረጎች አቀማመጥን መስተካከል ።

፮ኛ ፡ የአማርኛ ምሳሌ ሁኔታና አፈታት ።

ተራ ቁጥር	የአርእስቶች ማውጫ ፡	ገጽ
	የአማርኛ ምሳሌ ሁኔታና አፈ ታት	፫፪ - ፲፯፩
፯ኛ	ክፍል ፯	፲፯፪ - ፲፰፪
	ወርቃ ወርቅ ምሳሌ	
፰ኛ	ክፍል ፰	፲፰፫ - ፲፱፰
	የምሳሌዎች አጭር አፈታት	፲፱፱ - ፲፱፰
፱ኛ	ክፍል ፱	
	የግሥ ያታና ቁጥር በምሳሌ ዎች	፲፱፱ - ፪፻፩
፲ኛ	ክፍል ፲	
	የምሳሌዎች አሰካክ	፪፻፪ - ፪፻፫
፲፩ኛ	ክፍል ፲፩	
	የምሳሌዎች ሌላ ዓይነት አፈ ታት	፪፻፬ - ፪፻፯

መቅድም ፡

አስተማሪዎች ፡ ከዚያም ከዚህም እየቀሳሰሙ ፤ ባጠኑት ዕውቀታቸው ፡ ተማምነው ፡ ተማሪዎቻቸውን በሚገባ የሚያስተምሩት ፤ እንዲሁም ተማሪዎች ፡ የክፍል ትምህርታቸውን ከከባድነት የሚአቀልሉትና እንደ ልባቸውም ለማስፋፋት የሚችሉት ፤ እያነበቡ የሚያጠኑባቸውን ልዩ ልዩ የማስተማሪያና የመማሪያ መጻሕፍት በብዛት ሲያገኙ ነው ። መጻሕፍቱም የሚገኙት ፤ እያንዳንዱ የሀገሩ ተወላጅ ካለው ዕውቀቱ ላይ ፡ የሚቻለውን ያህል ድርሻ ድርሻውን እየሠራ ፤ ለሀገሩ ያበረከተላት እንደሆነ ብቻ ነው ። ሀገርም ተወላጆችዋ እንደየ ስጦታቸው መጠን የሚፈለግባቸውን ሥራ በደስታና በትጋት ከሠሩላት ፤ የወላድ መካን ከመሆን ትድናለች ።

አዘጋጂው ፡

ጽጌ ገብረ ኪዳን ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

መግቢያ ፤

፩ኛ የጎብር ቅኔና ሰም ለበስ ቅኔ ፤

የጎብር ቅኔ ፡ በመጨረሻው መሥመሩ ላይ ፡ የጎብር ቃልን ሳይጨምር ፤ ምን ጊዜም ቢሆን አይ ነገርም ፤ ሰም ለበስ ቅኔ ግን አብዛኛውን ጊዜ የጎብር ቃል ሳይገባበት ሊነገር ይችላል ፤ ይሁን እንጂ ፡ ሁለ ቱም የቅኔ ዓይነቶች የሚዘጋጁትና የሚነገሩት ፤ ዋና ውን ሐሳብ በመሸፈኛው ዓረፍተ ነገር ውስጥ እየደ በቁ ስለ ሆነ ፤ መንታ ሐሳቦችን አቁራኝተው የሚ ገኙ ቅኔዎች ናቸው ፤ ስለዚህ ፡ መሪ የሆነ አፈታታ ቸው በመጽሐፉ ውስጥ ተጽፎ ይገኛልና ፤ በማስተ ዋል ያነበቡትን ሰዎች ፡ ያጋጠማቸውን የጎብርና የሰም ለበስ ቅኔ ሁሉ ያለ አስተማሪ በጀ ሐሳቦች ለመፍታት ከማስቻሉም በላይ ፡ ባለ ቅኔዎችም እንደሚያደርጋ ቸው ፤ ጥርጥር የለውም ።

፪ኛ ማስተካከል ፡

አንዳንድ ባለ ቅኔዎች ፡ ቅኔን መቀኘታቸውን ብቻ እንጂ ፤ ቅኔው ከዘፈኑ ፡ ወይም ከዜማው ጋራ መስ

ማማት ፡ አለ መስማማቱን አያስታውሱም ፤ ስለዚህ እንደዚህ ያለውም የቅኔ ዓይነት ሲያጋጥም ፤ ለማስ ተካከል የሚያስችል ጥሩ ዘዴ ፡ በመጽሐፉ ውስጥ ይገኝበታል ።

፫ኛ ምሳሌዎች ፡

ምሳሌዎች ፡ በአሰካክ ግማሾቹ ፡ በስድ ዓረፍተ ነገር ደንብ ፡ ግማሾቹ በግጥም ዓረፍተ ነገር አኳኋን የተዘጋጁ ሲሆኑ ፤ በምሥጢር ደግሞ ፡ እኩሌቶቹ ውስጠ ወርቅ ወይም ሰም ለበስ ፡ የቀሩት ወርቃ ወርቅ ናቸው ። ስሜታቸውም ፈጥኖ ልብን የሚነካ ከመሆኑ የተነሣ ፡ ኢትዮጵያዊ የሆነው ሰው ሁሉ ፡ በጥል ጊዜ ጥለኞችን ለማስታረቅ ፡ በደስታ ጊዜ አድማጮችን ለማሳቅ ፡ በኃዘን ጊዜ ያዘኑትን ለማጽናናት ፡ በሙግት ጊዜ ዳኛውንና ተከራካሪውን ለማስረዳት ፡ በበደልም ጊዜ ጥፋተኛውን ለመገሠጽና ለመምከር ፡ እንደ ዚቅ አድርጎ እየመሰለና እየጠቀሰ ፤ እንደሚገለገልባቸው ለማንም የታወቀ ነው ። ከዚህም በቀር ምሳሌዎቹ ባጭር ባጭር ቁመት ተወስነው ስለሚነገሩ ፤ ከብዙ ዎቹ ላይ ፡ ጥቂት ጥቂት ቃሎች ይቀሩባቸዋል ፤ ስለዚህ ከኢትዮጵያውያን መካከል ላጋጠማቸው ነገር ፡ ምሳሌ ዎቹን እንደ ጥቅስ ጣል አድርገው በሚጠቀሙ ባቸው

ጊዜ ፤ ጠቅላላ ስሜታቸውን በሐሳብ ብቻ ሲያውቁት በንግግር ግን ፡ ምክንያቱን እያሞሉና ፤ ነገሩን እያተቱ በስድ ድርሰት መልክ ምሳሌውን ለመግለጽ የሚያቅ ታቸው ጥቂቶች አይደሉምና ፤ የመጽሐፉ መሰናዳት ከዚሁ ላይ የተመሠረተ ነው ።

ከዚህም ሌላ ፡ ከምሳሌዎቹ መካከል ፡ የፍቺ ወይም የሐሳብ ተመሳሳይነት ፡ የአነጋገር ትንሽ ልዩነት ፡ ያላቸው አያሌ ምሳሌዎች ስለሚገኙ ፤ በየወገን በየ ወገናቸው እየተለዩ ፤ እርስ በራሳቸው እንዲፋቱ ተደ ርገዋል ። ይህም የአፈታት አቋራጭ መንገድ መሆኑ ነው ።

ምዕራፍ ፩ ፡

ክፍል ፩ ፡

የጎብርና የሰም ለበስ ቅኔዎች ሁኔታና መደበኛ አፈታት ፤

ጥያቄ ፡ የአማርኛ የጎብርና የሰም ለበስ ቅኔዎች እን ዴት ያሉ ናቸው ፡-

መልስ ፡ የአማርኛ የጎብርና የሰም ለበስ ቅኔዎች በአ ንድ ዓረፍተ ነገርነት ብቻ እየተነገሩ በሁለት ዓረፍተ ነገሮች ተፈትተው ሁለት ሐሳቦችን የሚ ገልጹ ልዩ ንግግሮች ናቸው ።

ጥያቄ ፡ በ፪ ዓረፍተ ነገሮች የሚፈቱ ከሆነ ፤ ፩ኛውና ፪ኛው ዓረፍተ ነገሮች ምንና ምን ይባላሉ ፡-

መልስ ፡ ፩ኛው ዓረፍተ ነገር « ሰም » ፪ኛው ዓረፍተ ነገር «ወርቅ» ተብለው ይጠራሉ ።

ጥያቄ ፡ ፩ኛው ዓረፍተ ነገር « ሰም » ፪ኛው ዓረፍተ ነገር « ወርቅ » እየተባሉ የሚጠሩት በምን ምክ ንያት ነው ፡-

መልስ ፡ ፩ኛው ዓረፍተ ነገር «ሰም» መባሉ ለቅኔው ምሳሌ ወይም መሸፈኛ በመሆኑ ምክንያት ሲሆን ፤

ለምሳሌ የአማርኛ ቅኔ በመዲና ግጥም ፡

፩ኛ ፡ እንዳልዋጋ ፡ ቀንድ የለኝ ፤
እግዜር ጐዳ አርጎኝ ። (ጎብር)

ሰም ፡ እግዜር ጐዳ አድርጎ ስለ ፈጠረኝ ፤ እንዳልዋጋ ቀንድ የለኝም ።

ወርቅ ፡ እግዜር መናጢ ድኃ አድርጎ ስለ ፈጠረኝ ፤ እንዳልደሰት የተትረፈረፈ ሀብት የለኝም ።

፪ኛ ፡ የሐመር ጌታ ፡ ጌታም አንለው ፤
የሻንቆ ጌታ ፡ ጌታም አንለው ፤
የኛስ ጌታ ፡ የሠራን ነው ። (ጎብር)

ሰም ፡ የኛስ ጌታ የሠራን ፈረስ ጌታ ነው እንጂ ፤ የሐመር ፈረስ ጌታን ጌታ አንለውም ። እንዲሁም የሻንቆ ፈረስ ጌታን ጌታ አንለውም ።

ወርቅ ፡ የኛስ አምላክ የፈጠረን ፩ እግዚአብሔር ብቻ ነው እንጂ ፤ የአሕዛብን አምላክ ጣዖትን አምላክ አንለውም ። እንዲሁም የአስማተኞችን አምላክ ሰይጣንን አምላክ አንለውም ።

፫ኛ ፡ ማሳለፍማ ፡ ታውቃለህ ፤
አትሰጥም እንጂ ፡ ከጠላህ ። (ጎብር)

፪ኛው ዓረፍተ ነገር «ወርቅ» መባሉ ደግሞ ለቅኔው ዋናው ሐሳብ ከመሆኑ የተነሣ ነው ።

ጥያቄ ፡ የቅኔዎቹስ አፈታት እንዴት ነው ፡-

መልስ ፡ ፩ኛ ቅኔው ሲቀኝ ወይም ሲዘጋጅ ፤ በሰሙ የዓረፍተ ነገር ቃላት ብቻ ስለሆነ ፤ ወርቁ ዓረፍተ ነገር ፡ በሰሙ ላይ ውስጠ ታዋቂ ሆኖ ይቀራል ፤ ስለዚህ ሰሙ ዓረፍተ ነገር ሲያስፈልግ ለማብራራት ያህል ጥቂቶችን ቃላት ያስጨምራል እንጂ ፤ አብዛኛውን ጊዜ በፊት የተሳኩላትን ቃላት ብቻ እንደ ያዘ ይፈታና ፡ ፩ኛ ሆኖ ይጸፋል ።

፪ኛ ፡ እንዲሁም ወርቁ ዓረፍተ ነገር ፡ ብዙውን ጊዜ በሰሙ ቃላት ፈንታ ፡ ለወርቁ ባለቤት የሚስማሙትን ሌሎች ቃሎችን በመተካት እየተፈታ ፪ኛ ሆኖ ይጸፋል ፤ ይሁን እንጂ ፡ አንዳንድ ጊዜ ከሰሙ ቃላት ውስጥ ጥቂቶቹ በወርቅም ላይ ሊገቡ ይችላሉ።

፫ኛ ፡ ከዚህም በቀር ፡ በሰሙ ዓረፍተ ነገር ላይ የተነገሩ ተውሳከ ግሥ ፡ መስተዋድድ ፡ መስተፃምር ቃለ አጋንኖ ፤ የሚባሉት የሰዋስው ክፍሎች ቢኖሩ ፤ ሳይለወጡ ፡ ወይም ሳይቀነሱ ፤ እነርሱኑ ሊገቡ ይችላሉ ። ይህንንም ሁሉ ከዚህ በሚከተሉት ምሳሌዎች ለማረጋገጥ ይቻላል ።

ሰም ፡ ካንተ ጠላ እኔን ለሚመስሉት ሁሉ አታቀም ስም እንጂ ፤ ጠላ ማሳለፍንማ በደንብ ታውቃለህ ።

ወርቅ ፡ ሀብት መስጠትንማ በእርግጥ ትችላለህ ፤ ዳሩ ምን ይሆናል ! አንተ ካልፈቀድህ ፤ እኔን ለሚመስሉት ሁሉ ከማያልቀው ሀብትህ ላይ ፡ ምንም አትሰጥም ።

፬ኛ ፡ ከኔ ዘንድ ፡ የለም ተስፋ ፤
ዘራም ፡ እንደ በቀለ ጠፋ ! (ጎብር)

ሰም ፡ የዘራሁት ዘር እንደ በቀለ ወዲያው ስለ ጠፋ ፤ እንግዲህ ከኔ ዘንድ የአዝመራ ተስፋ የለም !

ወርቅ ፡ ዘሩ የሚባለው ወገኔ ፡ በቀለ እንደ ተባለው ዘመዴ ስለሞተ ፤ እንግዲህ ከኔ ዘንድ የወገን ብዛት ተስፋ የለም !

፭ኛ ፡ ጐንጆች ሲሳደቡ ፡ ለነገም አይሉ ፤
ስሂን በጸሎቱን ፡ ቆማጣ አሉት አሉ ! (ጎብር)

ሰም ፡ የጎንጅ ሰዎች ሲሳደቡ ፤ ለነገም አይሉ ፤ ምክንያቱም አቶ ስሂን በጸሎቱን እኮ አንተ ቆማጣ ብለው ሰደቡት አሉ !

ወርቅ ፡ የጎንጅ ሰዎች ሲናደዱ ምሕረት የላቸውም ፤ ምክንያቱም አቶ ስሂን በጸሎቱን እኮ ቆማ በሚባለው ቦታ ላይ ገድለው ጣሉት አሉ !

፮ኛ ፡ ሰው መላክ ፡ አይሆንም ብለው ፤
አልረዳ አለ ፡ ይህ ሰው ። (ጎብር)

ሰም ፡ ሰው ከቶ እንደ መልአክ ረቂቅ ሊሆን አይችልም ብዬ ላስረዳው ብሞክር ይህ ሰው ነገሩ አልገባ አለው ።

ወርቅ ፡ ምሥጢራችን እንዳይሰማ ራስህ ና እንጂ ፤ እኔጋ ሰውን አትላክ ብዬ ብመክረው ፤ ይህ ሰው በም ክሬ አልጠቀም አለ ።

፯ኛ ፡ ነፍሴ ለሥጋ ስትሳሺ ፤
ፍሪዳ መጣልሽ !

ሰም ፡ ነፍሴ ሆይ ! ብዙ ጊዜ ሥጋን መብላት ሲያምርሽ ፤ እነሆ አሁን ፡ ፍሪዳ መጥቶልሻልና ፤ እንግዲህ ደስ ይበልሽ !

ወርቅ ፡ ነፍሴ ሆይ! ሁል ጊዜ ለሥጋ ስታደሪ ፤ እነሆ ! አሁን የሰው ልጅ ዕዳ ሞት መጥቶብሻልና ፤ እንግዲህ መፍራት አለብሽ !

፰ኛ ፡ ከጐጃምና ከዳሞት ፤
የቱ ይበልጣል በስፋት ፡-

እኔስ በግምት ባየው ፤
ትልቁ ዳሞት ነው ።

ሰም ፡ ከጐጃምና ከዳሞት ፡ በስፋት የቱ ይበልጣል ፡-
እኔስ በግምት ባየው ፤ ትልቁ አገር ዳሞት ነው ፤
እላለሁ ።

ወርቅ ፡ ከማጣትና ከመሞት በጐጂነት የቱ ይበልጣል ፡-
እኔስ ባመዛዝነው ማጣት ዕዳው ገብስ ነው ፤
ትልቁ ዕዳ ግን ሞት ነው ፤ እላለሁ ።

ፀኛ ፡ ከዚያ ታች ያለችን ድውይ ፤
ከቶ ምን ቀመሽ አልሻት ወይ ፡-
ኋላ ጸጸቱ ባንቺ ይሆናል ፤
ተዪ ሥጋ ብለሽ ይሆናል !

ሰም ፡ ከዚያ ታች ያለችውን ሕመምተኛ ከቶ ምን ቀመስሽ አልሻት ወይ ፡- «ሥጋ አምሮኛል» ብላ ሽም እንደሆን ፤ ተዪ ስጫት ፤ አለበለዚያ ግን ኋላ ጸጸቱ ባንቺ ላይ ይሆናል !

ወርቅ ፡ ሰውነቴ ሆይ! ከሥጋሽ ጋራ ተዋሕዳ ያለች ውን ነፍስ በሰማይ ቤት የሚበጅሽን ሥራ ልሥ ራልሽ ፡- ከቶ አልሻት ወይ ፡- አለበለዚያም ይህ ሥጋሽ ፈራሽና በስባሽ ይሆናልና ፤ ተዪ ኋላ ዙኃኔው ባንቺ ላይ ብቻ ይሆናል !

ፀኛ ፡ አንድም ሰው የለ ፡ አስነሽ ፤
ሁሉም ፡ ቀብሮ ተመላሽ !

ሰም ፡ ሁሉም ሬሣውን በመቃብር ቦታ ላይ ቀብሮ ወደየቤቱ ተመላሽ ነው እንጂ ፤ ሟቹን ከሞት የሚያስነሣ አንድም ስንኳ የለም !

ወርቅ ፡ በዚህ ዓለም ላይ ሁሉም በሌላው ሰው ላይ ክፉ መካሪ የሌላውን ስም አጥፊ ነው እንጂ ፤ ለሰው ደግ ነገር የሚሠራ አንድም ስንኳ የለም !

ፀፀኛ ፡ ቀስቅሱትና ፡ ይናገር ፤
ተኛ አሁን ፡ እግዚአብሔር ።

ሰም ፡ አሁን እግዚአብሔር ተኝቶአልና ፤ ከእንቅልፉ ነቅቶ ይናገር ዘንድ ቀሰቀሱት ።

ወርቅ ፡ በክፋታችን ምክንያት አሁን ችላ ብሎናልና ፤ ይቅር ይለን ዘንድ ፡ «እግዚአብሔር ሆይ! እባክህን ከኛ ጋራ ሁን» እያላችሁ በጸሎት ለምኑት።

የአማርኛ ቅኔ በወል ግጥም ፡

ፀኛ በሽተኞች ብሎ ፡ ሰው እንዳይሸሻችሁ ፤
እባካችሁ ሰዎች ! አትተኙ ባልጋችሁ ፡- (ኅብር)

ሰም ፡ ሰዎች ሆይ ! ሰው በሽተኞች ናቸው ፤ ብሉ እንዳ ይሸሻችሁ እባካችሁ ሁል ጊዜ በአልጋችሁ ላይ አትተኙ ፡-

ንስ መረረኝ ! ይኸን ሰውየ ምን ባደርገው ይሻ ለኛል !

፬ኛ ፡ ጐንበስ ብሎ መኼድ ፡ አላቅ ብዬ እንደ ሰው ፤
እቀና ብዬ ነው ፡ ቤቱ የፈረሰው ! (ጎብር)

ሰም ፡ ወይኔ ! እንደ ሰዉ ጐንበስ ብሎ መኼድን ባለ ማወቄ የተነሣ ቤቱ የፈረሰው ቀና ብዬ እኮ ! በመኼዴ ነው !

ወርቅ ፡ ወይኔ ! እንደ ሰዉ ሁሉ ታግሼ በጋብቻ መኖር አቅቶኝ በቅንዓት ምክንያት ቤቱ ፈረሰ !

፭ኛ ፡ ጣፍጠኝ እንዳልበላ ፡ ይምረረው ብለኸኝ ፤
ምነው በሥጋ ሞት ፡ ጨምረህ ሰጠኸኝ ፡- (ጎብር)

ሰም ፡ መስጠትህ ካልቀረ ፤ እየጣፈጠኝ እንዳልበላውና ይምረረውም ብለህ ምነው በጥሬ ሥጋው ላይ ሐሞትን ጨምረህ ሰጠኸኝ ፡-

ወርቅ ፡ መፍጠርህ ካልቀረ ፤ በዚህ ዓለም ላይ ደስ ብሎኝ በሕይወት ሥጋ እንዳልኖርና እንዳልነበርኩም እንድሆን ምነው ሚች አድርገህ ፈጠርከኝ ፡-

፮ኛ ፡ ምን ያሉ ቁስ ናቸው ፡ ተዝካር የለመዱ ፤
አስታርቁኝ ብላቸው ፡ ፍታት ብለው ኼዱ ! (ጎብር)

ወርቅ ፡ ሰዎች ሆይ ! ሰው ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ፤ ብሎ እን ዳይነቅፋችሁ ፡ እባክችሁ በመንግሥታችሁ ሥራ ላይ አትለግሙ ፡-

፪ኛ ፡ ቸግሮኛልና ፡ ማኅበር ደርሶብኝ ፤
እባክህ ጌታዬ ! አሳልፍልኝ ፡- (ጎብር)

ሰም ፡ የማኅበር ድግስ ተራ ደርሶብኝ ፡ ቸግሮኛልና ፤ የኔ ጌታ ! እባክህን በዚያው ዕለት በጠላው ፡ ወይም በምግቡ አሳላፊነት እርዳኝ ፡-

ወርቅ ፡ አምላኬ ሆይ ! በዚህ ዓለም ላይ ድኸነት ተጭኖኝ በጣም ተቸግሬአለሁና ፤ እባክህን ሁሉንም በማይሳነው ችሎታህ ከድኸነት አውጣኝ ፡-

፫ኛ ፡ ዓምና ወባ ጥሎት ሳስታምም ከርሜ ፤
ባርያ ጣለው አሉ ! ምን ላርገው ደግሜ ! (ጎብር)

ሰም ፡ አምና ወባ ጥሎት መከራዬን አይቼ ሳስታም መው ከረምኩ ! ዘንድሮ ደግሞ « ባርያ ጣለው» አሉ ! አሁንስ መረረኝ ! ይኸን ሰውየ ምን ላርገው !

ወርቅ ፡ ዓምና በኔ በሚስቱ ላይ « ዕቅብት ይዟል » ቢሉኝ ፤ ታገሥኩት ፤ ቻልኩት ፤ ዘንድሮ ደግሞ ይግረምሽ ! ብሎ የባርያ ዕቅብት ያዘ ፤ አሉ ? አሁ

ኟኛ ፡ አንድ እግር በርበሬ ፡ መንቀል አቅቷችሁ ፤ አንድዶ ለብልቦ፡ አቃጥሎ ይፍጃችሁ! (ሰም ለበስ)

ሰም ፡ አንድ እግር በርበሬ ነቅሎ መጣል ካቃታቸኹ ፤ ስትበሉት ፤ አቃጥሎም ፡ ለብልቦም ይፍጃችኻ!

ወርቅ ፡ አንድ ሰው ብቻ የሆኑ አጼ ቴዎድሮስን ይዞ ማሠር ካቃታችሁ ፤ በእሳት አቃጥለው ወደ ገደል አስወርውረው ይጨርሷችኋ!

ታሪክ ፡

ጥንት በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በገዛ ፈቃዳቸው የተሾሙ ፭ ደጃዝማቾች ነበሩ ። እነርሱም ለያንዳንዳቸው የተከለለ ግዛትና የበላይ ገዥ ስላልነበራቸው ፤ አንዱ ቀለብተኛና ሸክም ሆኖ የሰነበተበትን ቀበሌ ለቆ ፡ ወደ ሌላው ሠፈር ሲሼድ አንዱ ባዲስ ሆድ ተተክቶ ይሠፍርበት ነበር ። በዚያም ጊዜ አንድ ባላገር ማንኛውንም ድግስ ቢያደርግ ፤ ከአዘጋጀው ድግስ ላይ የዓቅሙን ያህል ወስዶ በአቅራቢያው ለሚገኘው ደጃዝማች ብቻ ቢያበረክት ወይም ስላጋጠመው ነገር ወደ አንዱጋ ሼዶ አቤቱታውን ቢያቀርብ የቀሩት እንደ ናቃቸው ቁጥረውት ወታደሮቻቸውን አስከትለው በንዴት እየገሠገሱ ደርሰው በሰውነቱና በንብረቱ ላይ ጥቃት ሲያደርሱበት ብዙ ጊዜ ይኖሩ ነበር።

ሰም ፡ ወይ ጉድ ! የተዝካር ድግስና ዘኬን የለመዱ ምን ያሉ ቄስ ናቸው እቴ ! «ከባሌ ተጣልቻለሁና ፤ እባክዎን መምሩ ያስታርቁኝ» ብዬ ብለምናቸው ፤ እሽ ! ብሎ እንደ ማስታረቅ «ፍት ሐት አለብኝ!» ብለው ፡ ጥለውኝ ይሺዱ !

ወርቅ ፡ ወይ ጉድ ! ባልና ሚስትን ማፋታት የለመዱ ምን ያሉ ቄስ ናቸው እቴ ! «ከባሌ ጋራ ተጣልቻለሁና ፤ እባክዎን መምሩ ያስታርቁኝ » ብዬ ብለምናቸው ፤ ተቆጥቶ እንደ ማስታረቅ ፤ «ምንም አትሆንህም ! ወዲያ አብርራትና ዕረፍ !» ብለው ይሺዱ !

ኟኛ ፡ ሕመምተኛ ብትሆን ፡ ያመጣኋት ሚስት፤ አባት እናትዋ ቤት፡ ባልጋ መለስኳት ። (ጎብር)

ሰም ፡ የትዳር ጓደኛ ትሆነኝ ዘንድ ያመጣኋት ሚስት ሕመምተኛ ሆነችና በአልጋ ወስጄ ወደ አባት እናትዋ ቤት መለስኳት ።

ወርቅ ፡ የትዳር ጓደኛ ትሆነኛለች ብዬ ያመጣኋት ሚስት ፡ እሷስ ለካ የለመደች ኖራለች ! በኔም ላይ ባለገችና ፤ ወደ አባት እናትዋ ቤት ወዲያ መለስኳት ።

መቼም የግፍ ሥራ መስፈሪያው እስቲሞላ ድረስ ቢዘገይም እንኳ ፤ የማታ ማታ ሠሪውን ስለሚያጠፋው ፤ « አሁንስ ይዋጣልን» ብለው አንድ ቀን ጦርነት ገጠሙና ከአምስቱ መካከል ሦስቱ በጦር ሜዳ ሲሞቱ ሁለቱ ብቻ ተረፉ ። በዚያም ቀን ማታ እንደ አጋጣሚ ውሽንፍርና ነጐድጓድ የሌለበት ዝናብ ዘነበ ፤ ስለዚህ አንድ ባለ ቅኔ በማግሥቱ ከዚህ በኋላ ተጽፎ በሰምና ወርቅ የተፈታውን ሰም ለበስ ቅኔ ተቀኝባቸው ፤ ይባላል ።

፱ኛ ፡ ትናንትና ማታ ፡ መልካም ዝናብ ጣለ !
እንዲህ ቢደጋግም ፡ ጐመን በበቀለ ! (ሰም ለበስ)

ሰም ፡ ትናንትና ማታ እኮ መልካም ዝናብ ጣለ !
እንዲሁም ደጋግሞ ቢጥል ፤ ጐመን በበቀለ ነበረ !

ወርቅ ፡ ትናንትና ማታ ሕዝብ ያዘነባቸው ግፈኞች ሞቱ እኮ ! እንዲሁም የቀሩት ዓመፀኞች እየተከታተሉ ቢያልቁ ሰላማዊ ሰው ሁሉ በሰላም በኖረ ነበር !

፲ኛ ፡ የአዳኝን ተንኰል ፡ የማያውቅ ቆቅ ፤
በጥይት ተመቶ ፡ ይሆናል መረቅ ። (ሰም ለበስ)

ሰም ፡ የአዳኝን ዘዴ የማያውቅ ቆቅ ፡ በጥይት ተመትቶ ፡ ወይም በወጥመድ ተይዞ ፡ መልካም መረቅ ይሆናል ።

ወርቅ ፡ የወዳጅ ጠላትን ተንኰል የማያውቅ ሰው ፡ በሰብቅ ተጠልቶና ታሥሮ መሸሚያና መሸለሚያ ይሆናል ።

፲፩ኛ ፡ ከለከለን እንጂ ፡ ያ ክፉ አሳላፊ ፤
ደግሰው ነበረ ፡ ለሁሉም በሰፊ ! (ጎብር)

ሰም ፡ ያ ክፉና አድላዊ የሆነ አሳላፊ ከለከለን እንጂ ፤ እነሱስ ለሁሉም በሰፊው ድግስ አዘጋጅተው ነበር !

ወርቅ ፡ ያ ክፉና ጨካኝ የሆነ ሞት ከመካከላችን ነጥሎ ወሰደብን እንጂ ፤ እሱስ ለሁሉም ሰው በጣም ቸርና ደግ ነበረ !

፲፪ኛ ፡ ይኸን ወጥ ጓደኛሽ ፡ እኔ እንጃ መቅመሷን !
ዱሮም ጨው አትወድም ፡ አውቃታለሁ እሷን !
(ጎብር)

ሰም ፡ ጓደኛሽ ፡ ዱሮም ቢሆን ፡ ጨው የበዛበትን እንደማትወድ ፤ እሷን ዐውቃታለሁና ፤ ይኸን ወጥ ፡ እኔ እንጃ መቅመሷን !

ወርቅ ፡ ጓደኛሽ ፡ ከዱሮም ቢሆን ፡ ጨዋና ጭምትን እንደማትወድ ፤ እሷን ዐውቃታለሁና ፤ ይኸን የመረጥንላትን ሰው ፡ እኔ እንጃ ማግባቷን !

ታሪክ ፡

በአጼ ምኒልክ ጊዜ ከቤተ መንግሥት ባለሟ
ሎች መካከል አንዱ የሆኑ አለቃ ሣህሌ የተባሉ የአ
ንኮበር ሊቅ ነበሩ ። ከዕለታት አንድ ቀን የመስከረም
ወር በባተ በሦስተኛው ቀን ከአንኮበር አዲስ አበባ
መጡና እልፍኝ ገብተው አጼ ምኒልክን እጅ ነሥ
ተው እንዲቀመጡ ከተፈቀደላቸው በኋላ በንጉሠ
ነገሥቱ ዙፋን አጠገብ ቁጭ አሉ ። ወዲያው የሥጋ
ቤቱ ሹም ተጠርቶ ለእንግዳው እርጥብ ሥጋ እንዲ
መጣላቸው የሥጋ ቤቶችን ሹም አዘዙት ። ሹሙም
እሺ ብሎ እጅ ነሥቶ ወጣና በፍጥነትም ደርሶ ሥጋ
ቤቶቹን ቢያዛቸው « እረ ምንም የለም » አሉት ።
እርሱም ወዲያው ተመልሶ መጥቶ አጼ ምኒልክ
ዘንድ ጠጋ አለና በትሕትና አንገቱን ዝቅ አድርጎ
« ጃንሆይ ! ሥጋው አልቋል» አላቸው ። ሊቁም መል
ሱን እንደ ሰሙ ያን ጊዜውኑ ቀጠል አደረጉና የሚ
ከተለውን የጎበር ቅኔ በሥጋ ቤቱ ላይ ተቀኙባ
ቸው ይባላል ።

፲ኛ ፡ እምዬ ምኒልክ ፡ ሥጋ ቤቶችህን ፡ እንዳት
ቁጣቸው ።

ለመስቀል ብለው ነው ፡ የለም ማለታቸው ።

ሰም ፡ እምዬ ምኒልክ ሆይ ! ሥጋ ቤቶችህ ፡ አሁን

«ሥጋ የለም» ማለታቸው እንደ ዕንቁጣጣሽም
ለት ሁሉ ፡ እንዲሁም ለመስቀል በዓል ሰፊ
ድግሥ ማዘጋጀት ስላለባቸውና ቁጠባም ማድ
ረግ ስለሚገባቸው ነውና ፤ ሥጋ ቤቶችህን እን
ዳትቈጣቸው እለምናለሁ ፡- ማለት ነው ።

ወርቅ ፡ እምዬ ምኒልክ ሆይ ! ሥጋ ቤቶችህ አሁን
«ሥጋው እያለ የለም» ማለታቸው ፡ እንደ ተለ
መደው እንዲሁም ለራሳቸው ጥቅም ቋንጣ ሊያ
ደርጉ ሥጋውን እየዘለዘሉ ፤ በየገመዱ ላይ ለመ
ስቀል ስላሰቡ ነውና ፤ እባክህን ይቅር በላቸው
እንጂ ፤ አትቈጣቸው አትቅጣቸውም ፡ ማለት ነው ።

፲፩ኛ ፡ ዝናብ ደበደበን ፡ መጠለያም አጣን ፤
ጥላችንን ረስተን ፡ እዚህ ስለመጣን ! (ጎበር)

ሰም ፡ ጥላችንን ረስተን እዚህ ስለ መጣን ፤ መጠ
ለያ አጣንና ፤ ዝናብ እኮ ክፉኛ ደበደበን !

ወርቅ ፡ የጸብ ቂማችንን ረስተን ፡ እዚህ ቦታ ስለ
መጣንና ፤ ረዳትም ስላጣን ፤ ጠላታችን እኮ
አጠቃን !

፲፪ኛ ፡ ከብርዱ ላያድን ፡ ደግሞም ከዝናም ፤
ምንም ቢቸግረኝ ፡ ከዳስ አልገባም ! (ጎበር)

ሰም ፡ ከብርዱ ላያድነኝ ከዝናቡም ደግሞ ላያስጥለኝ
ምንም ቢቸግረኝ ፤ ከዳስ ውስጥ አልገባም ።

ወርቅ ፡ ከሐሳብና ከችግርም ውስጥ ላያወጣኝ ከሥ
ጋትም ላያድነኝ ምንም ቢችግረኝ ፤ ሠርቼ እበ
ላለሁ እንጂ ፤ ሌባና ቀማኛ ሆኜስ ከእሥር ቤት
ዕዳ ውስጥ አልገባም ።

ፕሼኛ ፡ የሠራሽው ቀይ ወጥ ፡ በጣም ጨው አነሰው ፤
እባክሽ ጨው አምጪ ፡- አንቺ ሰው አንቺ ሰው !
(ጎብር)

ሰም ፡ አንቺ ሰው ! የሠራሽው ቀይ ወጥ በጣም ጨው
አንሶት አልጫ (አለ ጨው) ሆኖአልና እባክ
ሽን ጨው ወዲህ በዪ ፡-

ወርቅ ፡ አንቺ ሰው ! ባንቺ አመራረጥ ብቻ ያገባሽው
ባል በጣም ቁም ነገርና ጨዋነት ያነሰው ሆኖ
አልና እባክሽን ጨዋ አማች አምጪ ፡-
ፕሼኛ ፡ የበረሃ አውሬዎች ፡ እዚህም አሉሳ !
ይህችው ተኩላ ፡ ነች ያችኛዋ አንበሳ ። (ጎብር)

ሰም ፡ እረግ ! የበረሃ አውሬዎች እዚህም አሉና ! ከነ
ዚህም ውስጥ የማታውቂት ቢኖር ይህችው
ተኩላ የምትባለዋ አውሬ ስትሆን ያችኛዋ ግን
ሴት አንበሳ ናት ።

ወርቅ ፡ እረግ ! እዚህም ሴትኛ አዳሪዎች አሉና !
ታዲያ እኮ ይህች ቆንጆ የመሰለችው ኩል ተኩላ

ነው ። ያችኛዋም ሌላ ነገር የመሰለችው ጥሩ ጥሩ
ለባብሳ ነው እንጂ ፤ ከባለ ትዳሮች በልጠው
አይደለም !

ፕሼኛ ፡ መኩራት መተማመን ፡ በውስጥም በደጅ ፤
በራስ ልጅ ይሻላል ፡ ከደጃዝማች ልጅ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ባገር ቤት ውስጥም ሆነ በአደባባይ ላይ ከደ
ጃዝማች ልጅ ይልቅ በራስ ልጅ መኩራትና
መተማመን ይሻላል ።

ወርቅ ፡ በደኅና ቀንም ሆነ በክፉ ቀን ከባዳ ልጅ
ይልቅ በወለዱት ልጅ መኩራትና መተማመን
ይሻላል ።

ፕዕኛ ፡ እኔስ ሀገሬ ላይ ፡ ቤትም አልሠራሁ ፤
በዳሞት መካከል ፡ ተቀምጫለሁ ።

ሰም ፡ እኔስ ዳሞት በሚባለው ሀገር መካከል ተቀ
ምጫለሁ እንጂ ፤ በትውልድ ሀገሬ ላይ ቤት
አልሠራሁም ።

ወርቅ ፡ እኔስ ሞት በተባለው የኃጢአት ዕዳ መካ
ከል ለጊዜው እኖራለሁ እንጂ ፤ የዘለዓለም ሀገሬ
በሆነው በሰማይ ቤት የሚያኖር መልካም ምግ
ባር አልሠራሁም ።

ሰም ፡ ፭ ዓመት ሙሉ በጣም የታመምነው ፤ዓድዋ ከተማ ላይ ይዞን የነበረው ተላላፊ በሽታችን አገርሽቶብን ነው ።

ወርቅ ፡ ከ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. የተ ሠቃየነው ፤ የዓድዋ ጦርነት ደመኛችን ፋሺስት አገራችንን ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት ለማድረግ ፈልጎብን ነው ።

ሯ፫ኛ ፬ ኪሎ ስኳር ፡ ይበቃል ስልሽ ፤
፮ ኪሎ ልግዛ ፡ ምነው ማለትሽ ፡- (ጎብር)

ሰም ፡ አራት ኪሎ ስኳር ይበቃል ስልሽ ፤ የለም ስድስት ኪሎ ነው የምገዛው ፤ ማለትሽ ለምን ድር ነው ፡-

ወርቅ ፡ ለቤትሽ ቅርብ ነውና ፤ አራት ኪሎ ከሚባ ለው ቦታ ስኳር ግዢ ስልሽ ፤ የለም ፤ ስድስት ኪሎ ከሚባለው ቦታ ሄጀ ነው የምገዛው ፤ማለ ትሽ ለምን ይሆን ፡-

ሯ፬ኛ ፡ ሁል ጊዜ ሲመቱ ፡ እኒያ ሴቶች ሁሉ ፤
አንቺስ አንዴ እንኳን ፡ አትመቺም አሉ !

ሰም ፡ እነዚያ ሴቶች ሁሉም ሁል ጊዜ ሲደበደቡ እንሰማለን ፤ አንቺ ግን አንድ ጊዜ እንኳን አል ተደበደብሽም አሉ ! እረ ምክንያቱ ምንድር ነው ፡-

ሯ፭ኛ ፡ ይኸን ያህል ሸክም ፡ ለምን ታነሻለሽ ፡-
እረ ተይ እረ ተይ! አንቺ ትቀጫለሽ ። (ጎብር)

ሰም ፡ አንቺ ልጅ ! ያለ ዓቅምሽ ይኸን ያህል ከባድ ሸክም ለምን ታነሻለሽ ፡- እረ ተይ እረ ተይ ! ቅጭት ይደርስብሻል ።

ወርቅ ፡ አንቺ ልጅ ! ይኸን ያህል ምክርና ተግሣጽ እየሰማሽ ለምን ሁል ጊዜ ታጠፊያለሽ ፡-
እረ ተይ ! እረ ተይ ! ከባድ ቅጣት ይደርስብሻል !

ሯ፮ኛ ፡ ሀብታሞች ደኽይተው ፡ በመለመናቸው ፤
የሰማቸው ገርሞት ፡ አየን ሲሰጣቸው ! (ጎብር)

ሰም ፡ ሀብታሞች ደኽይተው በመለመናቸው ምክን ያት ሲለምኑ ፤ የሰማቸውና ያያቸው ሁሉ እየ ተገረመ ሲመጸውታቸው አየን !

ወርቅ ፡ ጻድቆች ስለ ጽድቅ ሲሉ ደኽይተው ዘወትር ፈጣሪአቸውን በመለመናቸው ምክንያት ጣር ጋር የሌለበትን ገር የሆነ ሞትን ሲሰጣቸው አየን !

ሯ፱ኛ ፡ አምስት ዓመት ሙሉ ፡ በጣም የታመ ምነው ፤
ያድዋ በሽታችን ፡ አገርሽቶብን ነው ። (ጎብር)

ወርቅ ፡ እነዚያ ሴቶች ሁሉ ለባሎቻቸው ሁል ጊዜ ምቹዎች መሆናቸውን እንሰማለን ፤ አንቺ ግን ሳት ብለሽ እንኳን ለባልሽ ምቹ አይደለሽም አሉ ! እረ ምክንያቱ ምንድር ነው ፡-

ሯሯኛ ፡ ርስቴን በገዛ እጄ ፡ ማልማት አለብኝ ፤ ዓለም አለሁ ብሎ ፡ እንዳይወስድብኝ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ተጠማኙ ሰውየ ውሽቱን ቦታህን በደንብ አለማልህለሁ ፤ እያለ እንዳይነጥቀኝ ፡ ርስቴን በገዛ እጄ ማልማት አለብኝ ።

ወርቅ ፡ ኃላፊው የዓለም ደስታ ከዙኔ ላያድነኝ አለሁ ! አለሁ ! እያለ እንዳያታልለኝ ፡ የሰማይ ርስቴን መንግሥት ሰማያትን ለመውረስ በጎ ሥራን መሥራት አለብኝ ።

ሯኗኛ ፡ ምንም እንኳ ቢለኝ ፡ እሳት አልነድም ፤ ቆስቋሽና አናዳጅ ፡ እኔ አልፈልግም ። (ጎብር)

ሰም ፡ ማገዶው እርጥብ ሆኖ ምንም እንኳ እሳቱ እየ ተጨናበሰ አልነድም ቢለኝም ቅሉ ፤ እኔ ራሴ አነደዋለሁ እንጂ ፤ እሳቱን የሚቆሰቁስና የሚ ያያዝ ረዳት አልፈልግም ።

ወርቅ ፡ እኔ ሴተላጤ ፡ በመሆኔ ብቸኝነት ተሰምቶኝ ትዳር ቢያምረኝም ቅሉ ፤ ብቻዬን እኖራለሁ እንጂ ፤

ከጨዋነት ውጪ ሆኖ የሚያበሳጨኝን ባል በፍጹም አልፈልግም ።

ሯኗኛ ፡ ተሥሩ ቁረጡት ፡ ይኸን ዛፍ በቶሎ ፤ ጉዳት ሳያመጣ ፡ ድንገት ተገንጥሎ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ቅርንጫፉ ድንገት ገንጠል ብሎ ታላቅ ጉዳት ሳያመጣ በፊት ፤ ይኸን ዛፍ ተሥሩ ቁረጡት !

ወርቅ ፡ ሥር ሰድዶ ወዳጅ አበጅቶ ምሽጉን አጠን ክሮ ድንገት ታላቅ ጉዳት ከማምጣቱ በፊት ይኸን የውጭ ጠላት በቶሎ አባርሩት !

ሯኗኛ ፡ አሁን ይናደዳል ፡ ልብሱ ተበላሽቶ ፤ ጥላት ፡ ጥላት ! ሲሉት ፡ ፊት መስማቱን ትቶ (ጎብር)

ሰም ፡ እረ ጥላሽት ነካህ ! እያሉ ሲያስጠነቅቁት ፤ በፊት መስማቱን ትቶ ልብሱ ተበላሽና አሁን ይናደዳል ።

ወርቅ ፡ አብራት እንጂ ፤ አትያዛት እያሉ አስቀድመው ሲያስጠነቅቁትና ሲመክሩት ፤ በፊት ችላ በማለቱ መብቱ ተነክቶ ሀብቱ ጠፍቶ ከማያን ሠራራበት ሁኔታ ላይ ሲደርስ አሁን ይጨሳል ።

ሯፀኛ ፡ ጓደኛቸው ታሚል ፡ ማለትን ሰምተው ፤ ጠይቀውት መጡ አንቺንም አይተው ። (ጎብር)

ሰም ፡ ጓደኛቸው ታሚል ማለትን ሰምተው ፡ እሱ

ንም ጠይቀው አንቺንም አይተው መጡ ።

ወርቅ ፡ ጓደኛቸው ሴሰኛ ሆኖአል መባሉን ሰምተውና ራሳቸውም ነገሩን ተገንዝበው «ሌላው ይቅርና ዘመድ የሆንሽውን አንቺንም ስንኳ አይምርም» እያሉ አምተውት መጡ ።

ፀኛ ፡ ልዩ ልዩ ምግብ ፡ ምንም ቢኖር ባለም ፤
እንደ ሥጋ ከቶ ፡ የሚደግፍ የለም ። (ጎብር)

ሰም ፡ በዓለም ላይ ምንም እንኳ ልዩ ልዩ ምግብ ቢኖር ፤ እንደ ሥጋ ምግብ የሚያጠነክርና የሚ ያዳብር ከቶ የለም ።

ወርቅ ፡ በዓለም ላይ ምንም እንኳ ልዩ ልዩ ዘመድና ብዙ ባልንጀራ ቢኖርም ቅሉ ፤ እንደ ሥጋ ዘመድ ያለ ጥሎ የማይጥል ከቶ አይገኝም ።

ፀ፩ኛ ፡ እኖራለሁ እንጂ ፡ ከባል በትዳሬ ፤
እኔስ አልፈታም ፡ እንዳንቺ በወሬ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ከባሌ ጋር ተስማምቼ በትዳር እኖራለሁ እንጂ እኔስ እንዳንቺ ባል ባገባሁ በ፩ ወር ብቻ ተጠ ልቼና ተጣልቼ አልፈታም ።

ወርቅ ፡ እኔ ግን ከባል ፡ ከዘመድና ከጎረቤት ጋራ ተስማምቼ በጨዋነት እኖራለሁ እንጂ ፤ እንዳ ንቺ በአሉባልታና በወሬት አልጣላም ፤ አልበ ጣበጥም ።

ፀ፪ኛ ፡ ሱሪውን ሰፍቼ ፡ ብሰጠው ተካልኝ ፤
እሱም በማግሥቱ ፡ ጠቦት አመጣልኝ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ተካልኝ እንድሰፋለት ያመጣውን ሱሪውን ሰፍቼ ብሰጠው ፤ ጠበበውና እርሱም በማግሥቱ ተርትሬ እንደገና እንድሰፋው አመጣልኝ ።

ወርቅ ፡ ተካልኝ እንድሰፋለት ያመጣውን ሱሪውን በነፃ ሰፍቼ ብሰጠው ፤ ከትልቅ ውለታ ቆጠረ ውና ፤ እርሱም በማግሥቱ የበግ ጠቦት ስጦ ታን አመጣልኝ ።

ፀ፫ኛ ፡ ባሮጌ ቤት አንኑር ፡ ካባታችን ወርሰን ፤
አዲስ ቤት እንሥራ ፡ በቶሎ አፈራርሰን ። (ጎብር)

ሰም ፡ አሮጌውን ቤት ፍርስርስ አድርገን ፡ በማሻሻ ልና ጥሩ አቅድን በመስጠት አዲስ ቤት እንሥራ እንጂ ፤ ከአባታችን በወረስነው በአሮጌ ቤት ውስጥ አንኑር ።

ወርቅ ፡ የዱሮውን የእርሻ አያያዝ ተወት አድርገን በዘመናዊው የእርሻ ዘዴ የአገራችንን የኢትዮ ጵያን አፈር በቶሎ አርሰን ቁፍረን በሀብታችን እንጠቀምበት እንጂ ፤ ከአባቶቻችን በወረስነው በዱሮው አኳኋን ተወስነን አንኑር ።

ፀፀኛ ፡ ሥራ በዛ ብለሽ ፡ ሠርክ ስታኮርፊ ፤
ይኸው ባል መጣልሽ ፡ እንግዲህ ዕረፊ ! (ጎብር)

ሰም ፡ «የሥራ ቀን በጣም ስለ በዛ ደከምኩ» ! እያ
ልሽ ሠርክ ስትመረሪና ስታኮርፊ ፤ ይኸው !
የበዓል ቀን መጥቶልሻልና ፤ እንግዲህ እንደ
ልብሽ ዕረፊ !

ወርቅ ፡ «የጋብቻ ጊዜዬ ተላለፈብኝ ! ባል አጣሁ»
ብለሽ ሁል ጊዜ በዘመዶችሽ ላይ ስትዶሪሪ ፤
እነሆ ! ጥሩ ባል መጥቶልሻልና ፤ እንግዲህ
ደስ ይበልሽ !

ፀፀኛ ፡ አሳላፊዎቹን ፡ ምን አዘገያቸው ፤ አንተ
አሽከር ! በቶሎ ፡ ተወጡ በላቸው ! (ጎብር)

ሰም ፡ አሳላፊዎቹን ምን አዘገያቸው ! አንተ አሽከር !
በቶሎ ተወጡ አምጡ በላቸው !

ወርቅ ፡ ተበቃዮቹን ምን ያንቀላፋቸዋል ! አንተ
ልጅ ! ቁጭታችሁን በቶሎ ተወጡ በላቸው !

ፀፂኛ ፡ እስላምና አማራን ፡ ጠርቶ ነበር ካሣ ፤
ልጁን ክርስትና ፡ አክሱም ላይ ሲያነሣ ። (ጎብር)

ሰም ፡ ካሣ አክሱም ላይ ልጁን ክርስትና ሲያነሣ ፤
ለግብጣ እስላምና አማራን ጠርቶ ነበር ።

ወርቅ ፡ ወሬሣው ካሣ አክሱም ላይ የሚወደውን ሃይ
ማኖቱ ክርስትናን ከፍ ከፍ ለማድረግ ፡ እስላ
ምንና አማራን በሃይማኖት አንድ አድርጎአቸው
ነበር ።

ፀፂኛ ፡ ከሳሽ ቀርቦ ቆማል ፡ ፍርድ ቤቱም ጠራሽ ፤
ፈጠን ብለሽ ኺጂ ፡ አንቺ ልጅ ተከሳሽ ! (ጎብር)

ሰም ፡ አንቺ የተከሰሰሽ ልጅ ! የከሰሰሽ በዳኛው ፊት
ቀርቦ ቆሞአል ! ፍርድ ቤቱም ይጠራሻል !
እረ ፈጠን ብለሽ ኺጂ !

ወርቅ ፡ አንቺ ልጅ ! የነፃ ሐኪም ቤት ተርፏል !
የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤትም «ሕመም ሳይጸ
ናባችሁ ፤ ታከሙ ! » እያለ ይመክራል ! እንዲህ
የምትከሺ ከሆነ እረ ፈጠን ብለሽ ሐኪምጋ
ኺጂ !

ፀፂኛ ፡ ያደግሽበት ቆላ ፡ ጥሩ አገር መስሎሽ ፤
ደጋን አትናቂ ፡ እዚህ ቁጭ ብለሽ ! (ጎብር)

ሰም ፡ ያደግሽበት አገር ቆላ ስለሆነ ፤ ከሌላው አገር
የሚበልጥና በጣም ጥሩ አገርም መስሎሽ ፡ እባ
ክሽን እዚሁ ቁጭ ብለሽ ደጋ አገርን አትናቂ !

ወርቅ ፡ የተሟላ ሀብትና ማንኛውም ነገር በቤትዋ ሞልቶ ተርፎ እያለ እጅዋ አያርፍም ፤ ሌባ ናት ሲሉ ገና ዛሬ መስማቴ ነው ! ታዲያ ካልተቸገረችና ካላጣች ፤ የምትሰርቀው ለምን ይሆን ፡-

ሻይኛ ፡ አትቀላቅዱበት ፡ እረ ተዱ ! ስንላት ፤ ዐውቃ ነው ቅቤውን ፡ ያጠፋችው በላት !

(ጎብር)

ሰም ፡ ቅቤውን በላት ያጠፋችው ፤ « እረ ተዱ በቅቤው ላይ ላትን አትቀላቅዱበት ! » ስንላት ፤ እምቢ ብላ ነው ።

ወርቅ ፡ ባንተ ላይ የባለገችው ፤ « እረ ተዱ ! እንዲህ ያለው ሥራ አስነዋሪና ወንጀል ነው ፤ » ስንላትና ስንመክራት ፤ አልሰማ ብላ ስለ ሆነ ፤ ወድዳ እስክትጠላ ደብድባት !

ሻይኛ ፡ ያዘንን መጥፎነት ፡ ስታውቁ ሁላችሁ፤ ልጅቷ አላዘነች ፡ ለምን ትላላችሁ ፡- (ጎብር)

ሰም ፡ ሁላችሁም የኃዘንን መጥፎነትና ጐጂነት ስታውቁ ፤ ዘመድ በሞተ ቀጥር ፤ ልጂቷ ስለማታ ለቅስ ፤ «አላዘነችም» ብላችሁ ለምን ትጠሏት አላችሁ ፡-

ወርቅ ፡ በደጋን ጥጥ መንደፍን ፡ ፈትል መፍተልን ባለማወቅሽ ጥሩ ነገርና ሞያ መስሎሽ ፡ ሥራ በመፍታትም እዚሁ ተዘፍዝፈሽ እባክሽን ደጋንን አትናቂ !

ሻይኛ ፡ ተው አትናደድ ወልድ ! በዚህ በዓለም ፤ ተናዳጅ ሰው እንጂ ፡ አብ ግን አይሞትም ።

(ጎብር)

ሰም ፡ የሰው ልጅ ሆይ ! በዚህ ዓለም ላይ የማበሳጭ እንጂ ፤ የሚያበግን ሰው አይሞትምና ፤ እባክሽን በሆነውና ባልሆነው ነገር ተው አትናደድ !

ወርቅ ፡ የሰው ልጅ ሆይ ! ሥጋን የለበሰው እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ስለእኛ በሥጋ ሞት እንጂ ፤ እግዚአብሔር አብ ግን አልሞተምና ፤ በዚህ ዓለም ላይ ሳለህ በዚህ ምሥጢረ ሃይማኖት ረገድ እባክህን ተው አትጠራጠር !

ሻኛ ፡ እያለ በቤትዋ ፡ ውሃና ሳሙና ፤ እጅዋ አይጠራም ሲሉ ፡ ዛሬ ሰማሁ ገና !

(ጎብር)

ሰም ፡ ውሃና ሳሙና በቤትዋ ተርፎ እያለ እጅዋ ጭቅቅታምና እድፋም ነው ሲሉ ገና ዛሬ ሰማሁ ! እንዲህ ከሆነ የማትታጠበው ለምን ይሆን ፡-

ወርቅ ፡ ሁላችሁም የሕፃናትን ጠባይ ስታውቁ ፤ ሕፃ
ንዋ ባለቀሰች ቊጥር ፤ «አልቃሻ ነች» ብላችሁ
ለምን ትመረራላችሁ ፡-

ፍ፫ኛ ፡ መረብዋን ካገኘች ፡ እናት ኢትዮጵያ ፤
አያምራትም ዓሣ ፡ እንግዲህስ ወዲያ ። (ጎብር)

ሰም ፡ እናታችን ወ/ኢትዮጵያ ጠፍቶባት የነበረውን
መረብዋን ካገኘች ፤ ትጠቀምበታለችና ፤ እንግ
ዲህስ ወዲያ ዓሣ አያምራትም ።

ወርቅ ፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ፡ ከ፷ ዓመታት በላይ
ተለይታት የነበረችውን ጠቅላይ ግዛትዋን ኤር
ትራን ካገኘች ዘንዳ ፤ የተሟላች ሆናለችና እንግ
ዲህስ ወዲያ የባሕር በር ችግር የለባትም ።

ፍ፬ኛ ፡ ነነዌ ጾመ አሉ ፡ ሁሉም ተጸጸቶ ፤
ሕግን በመጣሱ ስለ ፈራ አብዝቶ ። (ጎብር)

ሰም ፡ የነነዌ ሕዝብ ሕገ አሪትን በመጣሱ ምክንያት
የመደምሰስ ቅጣትን ስለ ፈራ ፤ ሁሉም እየተ
ጸጸተ ፤ በሱባኤ ጾመ ፤ አሉ ።

ወርቅ ፡ የነነዌ ሕዝብ ፡ ሕገ - አሪትን በመሻሩ የተ
ነሣ ፡ እግዚአብሔር አብ ፡ በዮናስ አድሮ ክፉኛ
ዝቶበታልና ፤ በጣም ስለ ፈራ ፤ ሁሉም እየተ
ጸጸተ ፤ በሱባኤ ጾመ ፤ አሉ ።

ፍ፭ኛ ፡ መቼም ለሥራ ነው ፡ የተፈጠረው ሰው ፤
የሱስ ታመመልን ፡ እኛ እንጨርሰው ። (ጎብር)

ሰም ፡ መቼም ሰው የተፈጠረው ፤ ለሥራ ነውና ፤
ኢየሱስ የሥራውን እመም ታመመልን ዘንድ ፤
እኛ እየተሻማን እንጨርሰው ።

ወርቅ ፡ መቼም ሰው ፡ የተፈጠረው ፤ ለደስታ ብቻ
አይደለምና ፤ ኢየሱስ ለኛ ሲል መከራውን ከተ
ቀበለልን ፤ እኛም አርአያውን እንከተል ።

ፍ፮ኛ ፡ ተመርሬአለሁኝ ፡ በነዚህ ወራት ፤
እንቅልፍን ከልክላኝ ፡ ጉጉት የሚሏት ። (ጎብር)

ሰም ፡ ጉጉት የሚሏት ወፍ ሌሊት ሌሊት እየጮ
ኸች እንቅልፍን ከልክላኝ ፡ በነዚህ ወራት
በጣም ተመርሬ አለኹ ።

ወርቅ ፡ ፍላጐት የሚሉት ኃይለኛ ነገር ፡ ሌሊት
ሌሊት በሐሳብ ባሕር ውስጥ እያስዋኘ ፤ እንቅ
ልፍን አሳጥቶኝ ፡ በነዚህ ወራት በጣም ምርር
ብሎኛል ።

ፍ፯ኛ ፡ የባላባቱ ልጅ ፡ ደጅ ከጠና በጣም ፤
ወሎ ቢቀርበት ፡ የጁንስ አያጣም ።

ሰም ፡ የባላባቱ ልጅ ሳይሰለች ፤ በጣም ደጅ ከጠና ፤
ወሎ ቢቀርበት እንኳ ፤ የጁንስ የሚያጣ አይ
መስለኝም ።

ወርቅ ፡ ግፈኛው ባለ ሥልጣን ፡ ፍዳውን በቅርብ ጊዜ በእጥፍ ባይቀበልም እንኳ ፤ የማታ ማታስ የእጁን ያህል ሳይከፈለው እንደማይቀር አምና ለሁ ።

ሻጭኛ ፡ ባዶውን እንጀራ ፡ የበላኽ ሳላይ ፡
ከቤት ተርፎ እያለ ፡ ወጥ አትልም ወይ ፡- (ጎብር)

ሰም ፡ ወጥ ከቤት ተርፎ እያለ ፤ እኔ ሳላይና ሳላውቅ ባዶውን ወይም ደረቁን እንጀራ የበላኸው ፤ለም ንድር ነው ፡- ስለ ምንስ ወጥ ስጡኝ ፤ አትልም ነበር ፡-

ወርቅ ፡ ቆንጆና ጨዋ ሴት በሀገርህ ውስጥ ካልጠ ፋች ፤ ሚስት ሳታገባ ፤ ትዳርም ሳትይዝ ፤በወ ንደ-ላጤነት የምትኖረው ፤ ለምንድነው ፡- ስለ ምንስ ጥሩ ሴቶች አሉበት ጋ ወጣ ብለህ በመ ምረጥ አንዱን በሥርዓት አታገባም ፡-

ሻጩኛ ፡ ሥጋን ግዢ ቢሏት ፡ ሥጋን ካላጣች ፤
የሰው ዕቃም ወስዳ ፡ ሰብራዳ አመጣች ! (ጎብር)

ሰም ፡ ሥጋን ግዢ ብለው ቢልኳት ፤ በሥጋ መሸጫ ቤቱም ፡ ታላቅና ታናሽ ካላጣች ፤ እንዲሁም

በቤትዋ ውስጥ ማምጫ ዕቃ እያለ ፤ የሰውን ዕቃ ተውሳ ወሰደችና « ሰብራዳ » የሚባለውን ትንሽ ሥጋ ገዝታ አመጣች !

ወርቅ ፡ ሥጋን ግዢ ብለው ቢልኳት ፤ በሥጋ መሸጫ ቤቱም ታላቅ ታናሽ ተሰቅሎ እያየች፤ እንዲሁም በቤትዋ ውስጥ የሥጋ ማምጫ ዕቃ እያለ ፤ የሰውን ዕቃ ተውሳ ወስዳ ፡ ሰበረችና ዕዳ አመጣች !

ክፍል ፪ ፡

ቀላል የጎብር ቅኔ አፈታት ፤

ከዚህ በፊት ተጽፎ የሚገኘው የቅኔ አፈታት መደበኛ ሲሆን ፤ ከዚህ የሚቀጥለው ግን ፤ ቀላል የጎብር ቅኔ አፈታት ነው ። ይኸውም ከቅኔው ላይ የጎብር ቅኔ ቃሉን ብቻ ለይቶ መጻፍና ፡ በተራ ቍጥ ርም እየከፈሉ ፤ በሁለት ትርጉም ብቻ መፍታት ነው ።

ለምሳሌ ፡

ፈኛ ፡ ሸማዬን አጥቤው ፡ ያለሱ አንድ የለኝ ፤
ቶሎ እንዲደርቅልኝ ፡ ሲያስብ ነው መሰለኝ ፤
ዐዋቂው ወንድምህ ፡ ከድንጋይ አስጣለኝ ።

ከድንጋይ አስጣለኝ ፡

፩ኛ ከድንጋይ አስጣው አለኝ ፡
፪ኛ በድንጋይ ከመወገር አዳነኝ ።
፪ኛ ፡ እንግዲህ ቂማችሁ ፡ ፈጽሞ ይረሳ ፤
ከታረቃችሁ ዘንድ ፡ ወድዳችሁ በካሣ ።

በካሣ ፡

፩ኛ ካሣ በሚባለው ሽማግሌ ፤
፪ኛ በበደል ዋጋ ።
፫ኛ ፡ ታስተውልኻለች ፡ ክፉኛ ተቀምጣ ፤
ተጣፋጩ ክፍል ፡ ቶሎ ቶሎ ውጣ !

ውጣ ፡

፩ኛ መሰስ በል ፤
፪ኛ ፡ ሰልቅጣ ።
፬ኛ ፡ ጌታ የእንጀራ ቤት ፡ እኔን አትርሳኝ ፡-
አልጠገብኩምና ፡ ዳረጎቴ አንጣኝ ።

አንጣኝ ፡

፩ኛ ፡ ትንሽ ሆናብኝ ፤
፪ኛ ፡ ከፍ ከፍ አርገኝ ።

፭ኛ ፡ እንግዲህ ትቀጣ ፡ አጠቃት በሽታ !
ራስዋ ካመጣችው ፡ ወድዳ ተመኘታ ።

ተመኘታ ፡

፩ኛ ፡ እየተመኘች ፤
፪ኛ ፡ ከመኘታ ላይ ።

፮ኛ ፡ ከዳተኞችና ፡ ያፍ ወዳጆች ናቸው ፤
ይኸ ብቻ አይደለም ፡ ብዙ ነው ጉዳቸው !

ጉዳቸው ፡

፩ኛ ፡ የነሱ ጉድ ፤
፪ኛ ፡ ጉዳት አድርስባቸው ።

፯ኛ ፡ እንዳሽከር በመቆም ፡ ወገቤ እስቲሰበር ፤
ስጥ ጠብቅ ባትዪኝ ፡ አልሸሽም ነበር ።

ስጥ ጠብቅ ፡

፩ኛ ፡ የተሰጣውን ጠብቅ ፤
፪ኛ ፡ ስጠኝ ፤ ክፈል ፤ ወረፋ ጠብቅ ።

፰ኛ ፡ እንዲህ የሳቁበት ፡ በማያቅ ብሳና ፤
እነርሱስ ቢሆኑ ፡ መቼ አስታወቁና ።

መቼ አስታወቁና ፡

፩ኛ ፡ አስታ የሚባለውን መቼ ዐወቁና ፡-
፪ኛ ፡ ማስታወቂያውን መቼ አሰሙ ፡-
፬ኛ ፡ በሰዋስው ሥርዓት ፡ እንደ ተማርነው ፤
ይሁን እንጂ እንዳትል ፡ አፍራሽ እኮ ነው !

አፍራሽ ፡

፩ኛ ፡ ተቃራኒ ፤ የሚያፈርስ ።
፪ኛ ፡ አንቺን አፍራ ።
፫ኛ የያዝሽው ጆንያ ፡ ለዚያ እህል አይበቃ ፤
ለምን ትኼጃለሽ ፡- አንቺ ልጅ ያለቃ ።

ያለቃ ፡

፩ኛ ያለ ዕቃ ፤
፪ኛ ፡ የሹም ።
፲፩ኛ ፡ የማያውቅ የለም ፡ አንድ ሰውም ከኛ ፤
ለማስተዳደርዋ ፡ ብዙ ሠራተኛ ።

ለማስተዳደርዋ ፡

፩ኛ ፡ ሹም ለመሆንዋ ፤
፪ኛ ፡ ከየወንዱ ጋር ላዳር ብቻ መኼድዋ ።
፲፪ኛ ፡ ከተማሮች ሁሉ ፡ አንቺ ራስ አለሽ ፤
ሁሉን ለመጨረስ ፡ ምንም አልቀረሽ !

ሁሉን ለመጨረስ ፡

፩ኛ ፡ ትምህርቱን ሁሉ ለመጨረስ ፤
፪ኛ ፡ ወንዱን ሁሉ ለማዳረስ ።
፲፫ኛ ፡ ሊደበቅ ወይ ሊካድ ፡ የማይቻለው ፤
ርዝመቱም ቅጥነቱም ፡ ከዘራችን ነው ።

ከዘራችን ፡

፩ኛ ፡ ከእኛ ዘር ፤
፪ኛ ፡ የእኛ ከዘራ ።
፲፬ኛ ፡ ይችን ላም ለመግዛት ፡ በጎያ ብመኝ ፤
ደላለው ግን አለኝ ፡ ያለ ዓርባ አትገኝ ።

ያለ ዓርባ ፡

፩ኛ ፡ ያለ አርባ ብር ፤
፪ኛ ፡ ያለ ዓርብ ቀን ።
፲፭ኛ ፡ ስድስት መቶ ብር ፡ እንደ ተበደረች ፤
ሸመጠጠች እንጂ ፡ አምና እኮ ነበረች !

አምና ፡

፩ኛ ፡ ትቀብላ ፤
፪ኛ ፡ ባለፈው ዓመት ።
፲፮ኛ ፡ የነሳሽኝ ብዕር ስለጠፋብሽ ፤
እሰይ ደስ ብሎኛል ! ባልተገኘልሽ !

ባልተገኘልሽ ፡

ልኛ ፡ እንደጠፋ በቀረ !
ይኛ ፡ ባል መጣልሽ ።
ፕኟኛ ፡ ያቺ ጋጋሪያችን ፡ ዛሬ ምን ነካት ፤
አታውቅም ነበረ ፡ እንጀራ አሮባት ፡-

እንጀራ አሮባት ፡

ልኛ ፡ እንጀራ አቃጥላ ፤
ይኛ ፡ እንጀራ አጥታ ።
ፕኟኛ ፡ አንቺ እያጫወትሽው ፡ እሱ ሲላጨኝ ፤
ሺጂ ፡ ብዬሻለሁ ፡ ስላስቄረጥሽኝ ።

ስላስቆረጥሽኝ ፡

ልኛ ፡ በቁሙ ቀሪ ፤
ይኛ ፡ ስለ አስጨከንሽኝ ።
ፕበኛ ፡ ቀበቶዬን ጠብቅ ፡ ብሎ ካልነገረኝ ፤
ታጥቃው ትኺድ እንጂ ፡ እኔ ምንችገረኝ !

ታጥቃው ፡

ልኛ ፡ ሸብ ታድርገው ፤
ይኛ ፡ ጥቃት ታድርስበት ።
ፏኛ ፡ በየቀኑ ወጥቶ ፡ ሰዎች እንዲሻሙት ፤
ጋዜጣውን ልጄ ! በፍጥነት አትሙት ።

አትሙት ፡

ልኛ ፡ እንዲታተም አድርጉ ፤
ይኛ ፡ ሞት አይነካህ ።
ፏ፭ኛ ፡ እንዳያልቁባችሁ ፡ እንዳይጨረሱ ፤
እኒያን በጎቻችሁ ፡ ውሰዷቸው ከሱ ።

ከ ሱ ፡

ልኛ እየ ከሱ ኼዱ ፤
ይኛ ፡ ከእርሱ ዘንድ ።
ፏይኛ ፡ አማቼ ነው እኮ ! ትናንት ያየነው ፤
ማጣት አለው እንጂ ፡ መልኩስ ጥሩ ነው ።

መልኩስ ፡

ልኛ ፡ የሱስ መልክ ፤
ይኛ ፡ መነሱሴ ሁን ።
ፏ፫ኛ ፡ መሸከሙ ይቅርብህ ፡ ይህን ልጅ ስለው ፤
እዚህ ላይ ነው እኮ ! ጋኔን የጣለው ።

ጋኔን ፡

ልኛ ፡ የኔን ጋን ፤
ይኛ ፡ ሰይጣን ።
ፏ፬ኛ ፡ መጽሐፍን ለመግዛት ከኼድክልን አንተው ፤
ሌላው እንኳን ቢቀር ፡ ታሪኩን አትተው ።

አትተው ፡

፩ኛ ፡ መተው የለብህም ፤
፪ኛ ፡ አስፋፋው ።
፫ኛ ፡ ወዲህ ፍጹም ጨዋ ፡ ወዲህ ጌታ ናቸው ፤
ለራስዋ ተጐዳች ፡ ብትወጣ ከሳቸው ።

ከሳቸው ፡

፩ኛ ፡ ከእርሳቸው ጋ ፤
፪ኛ ፡ እርሳቸውን ከስሳ ።
፫ኛ ፡ መሐንዲስነቱን ፡ ከተማርከውማ ፤
ኺድ አንተ ቀይሰው ! አዲሱን ከተማ ።

ቀይሰው ፡

፩ኛ ፡ ሸንሽነው ፤
፪ኛ ፡ ቀይ የሆንህ ሰው ።
፫ኛ ፡ ስትጠባበቂ ፡ መረብሽን ጥለሽ ፤
መቆየት ደግ ነው ፡ ዓሣ አለፈልሽ !

ዓሣ አለፈልሽ ፡

፩ኛ ፡ ዓሣ አገኘሽ ፤
፪ኛ ፡ ቀን ወጣልሽ ።
፫ኛ ፡ ተዛምዶ እኮ ሞላው ! እስተመካከል ፤
ይህ ነጭ ሴት አኩሪ ፡ እዚህ ቢተከል !

ነጭ ሴት አኩሪ ፡

፩ኛ ፡ ነጭ ሴት አኩሪ የሚባል የአበባ ተክል
፪ኛ ፡ ሴት አምላኩ ፈረንጅ ።
፫ኛ ፡ በሬ አርደኻልና ፡ ባንስተኛው ዋጋ ፤
ለኔም ለልጆቼም ፡ እባክህን ሥጋ ፡-

ሥጋ ፡

፩ኛ ፡ በቁሙ ቀሪ ፤
፪ኛ ፡ አስብ ።
፫ኛ ፡ እረ እናንተ ሰዎች ! ጭዴን ያጠፋችሁ ፤
ማንስ ማን በማጭድ ፡ ሲጫወት አያችሁ ፡-

በማጭድ ፡

፩ኛ ፡ በማን ጭድ ፡- በማን ገለባ ፡-
፪ኛ ፡ ማጭድ በሚባለው ብረት ።
፫ኛ ፡ ሐሳብ ነው ብትሉ ፡ እንቅልፍ የነሣው ፤
የምለውስ እኔ ፡ ያቡናችሁ ነው ።

ያ ቡናችሁ ፡

፩ኛ ፡ ያ የናንተ ቡና ፤
፪ኛ ፡ ቡን ያርጋችሁ !

ክፍል ፫ ፡

የጎብር ቃሎች አፈታት ፤

የጎብር ቃሎች ፡ በቅኔ ውስጥ ገብተው ሲነገሩ ፤ በሁለት ፍቺዎች ብቻ ተወስነው ይተረጐማሉ ፤ ምክንያቱም ፡ ቅኔው ፡ «ሰም ፡ ወርቅ» እየተባለ ፤ በሁለት ሐሳቦች ብቻ እንጂ ፤ ከሁለት ሐሳቦች በላይ ሊፈታ ስለማይቻል ነው ። ይኸንንም ከዚህ በፊት በተጻፈው የጎብር ቅኔ አፈታት ሁሉ ለማረጋገጥ ይቻላል ፤ የጎብር ቃሎች ብቻቸውን በሚነገሩበት ጊዜ ግን ፤ በሁለትና ከሁለት ፍቺዎችም በበለጠ ሊተረጐሙ ይችላሉ ።

ለምሳሌ ፡ የጎብር ቃሎችና ፍቺዎቻቸው ፤

ባሌ ፡

፩ኛ የኔ ባል ፤
፪ኛ ያገር ስም ።

ገርሞት ፡

፩ኛ ደንቆት ፤
፪ኛ ገር የሆነ ሞት ።

ታፋቸው ፡

፩ኛ የነሱ ታፋ ፤
፪ኛ ከነሱ አፍ ።

ክሳት ፡

፩ኛ መክሳት መጐዳት ፤
፪ኛ እሷን ክሳ ።

ቅመሽው ፡

፩ኛ ቀመስ አርጊው ፤
፪ኛ ቃም አርገሽው ።

አለቃ ፡

፩ኛ ዕቃ ሳይኖር (ያለ ዕቃ)
፪ኛ የበላይ ።

አላቅም ፡

፩ኛ አላውቅም ፤
፪ኛ ዓቅም ሳይኖር ።
(ያለ ዓቅም)

ብልስ ፡

፩ኛ ላስ ባደርግ ፤
፪ኛ ብናገርስ ፤
፫ኛ ቅልስ ፡ ተባይስ ።

እሥር ፡

፩ኛ ከታች ከሥር ፤
፪ኛ የታሠረ ።

በጃቸው ፡

፩ኛ ጠቀማቸው ፤
፪ኛ በነሱ እጅ ።

ተሥጋ ፡

፩ኛ ከሥጋ ላይ ፤
፪ኛ ተሰክታ ።

ትመቻለሽ ፡

፩ኛ ትደበደቢ አለሽ ፤
፪ኛ ምቹ ነሽ ።

ተግቼ ፡

፩ኛ ትጉህ ሆኜ ፤
፪ኛ እየተጋትኩ ።

ዛሬ ፡

፩ኛ ይህ ቀን ፤
፪ኛ የኔ ዛር ።

ልል ነው ፡

፩ኛ ልናገር ነው ፤
፪ኛ የላላ ነው ።

ስል ፡

፩ኛ ስናገር ፤
፪ኛ የተሳለ የሰላ ።

ባላት ፡

ፏኛ በዓላት ፤
ፔኛ በደበደባት ፤
ፕኛ በነገራት ።

አይገድም ፡

ፏኛ አይችገርም ፤
ፔኛ ገዳም አይሁን ።

ተዋጋው ፡

ፏኛ ግጠመው ፤
ፔኛ ከሱ ዋጋ ። (ከዋጋው)

የሰው ገለባ ፡

ፏኛ የሰው የኾነ ገለባ ፤
ፔኛ ቀላል ሰው ።

ሳምናት ፡

ፏኛ ሳም አረግናት ፤
ፔኛ እያመንኳት ።

ሳንቃቸው ፡

ፏኛ የነሱ ሳንቃ ፤
ፔኛ እነሱን ሳንቅ ።

ራሳቸሁ ፡

ፏኛ ራስ አላቸሁ (በሰበሳ ቸሁ)
ፔኛ በገዛ እጃቸሁ ።

ደፍራሽ ፡

ፏኛ የሚደፈርስ ፤
ፔኛ አንቺን ደፍራ ።

ገብስማ ፡

ፏኛ ገብስን የሚመስል ፤
ፔኛ ገብስስ ። (ገብስ ማን)

ፈትነሽ ፡

ፏኛ ከፈተንሽ በኋላ ፤
ፔኛ የተፈታሽ ነሽ ።

ላም ናት ፡

ፏኛ ላም ነች
ፔኛ አምናት ዘንድ ።

ተኛ ፡

ፏኛ ጋደም በል ፤
ፔኛ ከኛ ጋር ።

ባባ ፡

ፏኛ በአባ ፤
ፔኛ ተሸበረ ።

ወይ በለው ፡

ፏኛ ወይ ምታው ፤
ፔኛ አቤት ! በለው ።

ግርድ ፡

ፏኛ ያልተጣራ ፤
ፔኛ የተጋረደ ።

ላብላሽ ፡

ፏኛ አበላሽ ዘንድ ፤
ፔኛ ላብን የሚልስ ።

ደብተራችሁ ፡

ፏኛ የናንተ ደብተራ ፤
ፔኛ የናንተ ደብተር ።

ገላችሁ ፡

ፏኛ የናንተ ገል ፤
ፔኛ የናንተ ገላ ።

ላማቸው ፡

ፏኛ የነሱ ላም ፤
ፔኛ አማቸው ዘንድ ።

ያቃል ፤

ፏኛ ያውቃል ፤
ፔኛ ቃሉ ።

ላይ ነው ፡

ፏኛ ልመለከት ነው ፤
ፔኛ ከላይ ነው ።

በልተው ፡

ፏኛ ተመግበው ፤
ፔኛ አታድርግ ።

በጋ አይወድም ፡

፩ኛ በማን አይፈቅድም ፤
፪ኛ በጋን (ሐጋይን አይ
ወድም) ።

መክሰስ ፡

፩ኛ ማቆያ ፤
፪ኛ ክስን ማቅረብ ።

ብረታቸው ፡

፩ኛ የነርሱ ብረት ፤
፪ኛ የረታኋቸው እንደ
ሆን ።

ሳጠራ ፡

፩ኛ ቅርጫት ፤
፪ኛ እያጣራሁ ።

ምራት ፡

፩ኛ እንድትመራት ይሁን፤
፪ኛ የመጀመሪያ ሚስት ፤
፫ኛ ይቅር ብላት ።

አባባሱባት ፡

፩ኛ አበረቱባት ፤ (አከረሩ
ባት)
፪ኛ አባ ክፉባት ።

ክዳን ፡

፩ኛ መክደኛ ፤
፪ኛ እኛን ክዳ ።

ማርኩት ፡

፩ኛ ይቅር አልኩት ፤
፪ኛ ምርኮኛ አድርጉት ።

በልሁ ፡

፩ኛ የሰው ስም ፤
፪ኛ በሱ እልክ ።

ዕርድ ፡

፩ኛ የታረደ ፤
፪ኛ ምሽግ ፤
፫ኛ ቅመም ። (ብጫ)

ከታች ፡

፩ኛ የሚያስገባ ፤
፪ኛ ከሥር ፤
፫ኛ የሚሰበሰብ ።

ቀናሽ ፡

፩ኛ ቀጥ አልሽ ፤
፪ኛ ሆነልሽ ፤
፫ኛ የሚቀንስ ፤
፬ኛ ቅንዓት አደረብሽ ።

ጦራቸው ፡

፩ኛ የነሱ ጦር ፤
፪ኛ ጧሪ ሆናቸው ።

ማታ አይመጣም ፡

፩ኛ በምሽት አይመጣም
፪ኛ መዓት አይመጣም ።

ከተማ ፡

፩ኛ መሸበሰቢያ ፤
፪ኛ መጨረሻ ።

አብነት ፡

፩ኛ አባትነት ፤
፪ኛ መድኃኒት ፤
፫ኛ አርአያ ።

አትሙት ፡

፩ኛ እንዲታተም አርገት ፤
፪ኛ ሞት አይንካህ ፤
፫ኛ በክፉ አታንሱት ።

ቀሰል ፡

፩ኛ ቁእያልኩ ስቆጥር ፤
፪ኛ የቆሰለ ።

ስማ ፡

፩ኛ አድምጥ ፤
፪ኛ ለጭልጫ ።

አላጣላቸውም ፡

፩ኛ እንዲጣሉ አላደርግም ፤
፪ኛ አገኘላቸው ።

ጉብል ፡

ልኛ ጉ ብዬ ብናገር ፤
ይኛ ልጅ ።

አያክም ፡

ልኛ አይፈውስ ፤
ይኛ አይፎክትም ።

ነቃሽ ፡

ልኛ ምስክር ፤
ይኛ የሚያሞደጉድ ፤
ቮኛ አሸጐርጓሪ ።

ላጫት ፡

ልኛ ላጥ አርጊአት ፤
ይኛ እንዳጫት ፤
ቮኛ ልጭት አርጊአት ።

ና ተኛ ፡

ልኛ ናና ጋደም በል ፤
ይኛ ከኛ ጋራ ና ።

ብላ ፡

ልኛ ተናግራ ፤
ይኛ ተጋበዝ ።

ምሳችሁ ፡

ልኛ ቆፍራችሁ ፤
ይኛ የናንተ ምሳ ።

ቀፈው ፡

ልኛ ለምነው ፤
ይኛ አስቀይመው ፤
ቮኛ አፍፈው ።

አሰላ ፡

ልኛ አተባ ፤
ይኛ የከተማ ስም ፤
ቮኛ አጠቀሰ ።

አበል ፡

ልኛ አን ፡ ጥራ ፤
ይኛ ድርሻ ።

ግብር ፡

ልኛ ሥራ ፤
ይኛ ደግስ ።

ዕጣ ፡

ልኛ አታግኝ ፤
ይኛ ዕድል ።

ሳይ ፡

ልኛ ሥእል ሠሪ ፤
ይኛ አፋጭ ፤
ቮኛ እያየሁ ፤
ዮኛ እሁ ! እሁ ! ባይ ።

ብስል ፡

ልኛ የበሰለ ፤
ይኛ ባፋጭ ፤
ቮኛ ሥዕል ብሠራ ፤
ዮኛ ኡሁ ኡሁ ! ብል ።

ሥጋ ፡

ልኛ ብርንዶ ፤
ይኛ አስብ ፤
ቮኛ ሸጉጣ (ሰክታ፡ሸንቅራ)

አምራ ፡

ልኛ ተውባ ፤
ይኛ አቅና ።

ላያት ፡

ልኛ ለአያት ፤
ይኛ አያት ዘንድ ።

አማሽ ፡

ልኛ አሚቂ ፤
ይኛ በጥባጭ ፤
ቮኛ በክፉ አነሣሽ ፤
ዮኛ አሳምማሽ ።

እርዳቸው ፡

ልኛ የነሱ ምሽግ ፤
ይኛ እነሱ ያረዱት ፤
ቮኛ የነሱ ቅመም ፤
ዮኛ አግዟቸው ።

አይክትም ፡

ልኛ አያስገባም ፤
ይኛ ከተማ አይሁን ፤
ቮኛ አይሰበሰብም ።

ልጣቸው ፡

ፏኛ አላግኛቸው ፤
ፔኛ የነሱ ልጥ ፤
ቮኛ ሞሽልቃቸው ።

የለሽም ፡

ፏኛ አልተገኘሽም ፤
ፔኛ አላገኘሽም ።

ገላጋይ ፡

ፏኛ አስታራቂ ፤
ፔኛ ሸክላ ተኳሽ ።

ተበሉ ፡

ፏኛ ከበሉ ዘንድ ፤
ፔኛ ተላመጡ ።

ሥራ ሥሩ ፡

ፏኛ ሥራን ሥሩ ፤
ፔኛ ሥራ ሥር ።

በጠላችሁ ፡

ፏኛ በናንተ ጠላ ፤
ፔኛ ጥልት ባደረጋችሁ ።

ጠበቶ ፡

ፏኛ ገፍፎ ፤
ፔኛ ነጣቶ ፤
ቮኛ መግምጎ ።

ዘርፋፋ ፡

ፏኛ ዘር በዛ ፤
ፔኛ የሚንዘረፈፍ ።

ጋኔን ፡

ፏኛ የኔን ጋን ፤
ፔኛ ሰይጣን ።

ስሜን ፡

ፏኛ የኔን ስም ፤
ፔኛ የአገር ስም ።

ስጥ ፡

ፏኛ ለግስ ፡ አትከልክል ፤
ፔኛ የተሰጣ ።

በወሬ ፡

ፏኛ በኔ ወር ፤
ፔኛ በአሉባልታ ።

ብላሽ ፡

ፏኛ ከንቱ ፤
ፔኛ ነግራሽ ።

አዞ ፡

ፏኛ ትእዛዝን ሰጥቶ ፤
ፔኛ የባሕር አውሬ ።

ተከፍቶ ፡

ፏኛ ክፍቶ ሆኖ ፤
ፔኛ አዝኖ ።

ተሰጥቶ ፡

ፏኛ ተዘርሮ ፤
ፔኛ የተሰጠ ፡ ተቀብሎ ።

አትተው ፡

ፏኛ መተው የለብህም ፤
ፔኛ አስፋፋው ።

ቀይሰው ፡

ፏኛ ቀይ የሆነ ሰው ፤
ፔኛ ሸንሽነው ።

አርጊው ፡

ፏኛ እንዲረጋ አድርጊው
ፔኛ ሥሪው ።

ሰኔ ፡

ፏኛ ፰ኛው ወር
ፔኛ የኔ ሰን ።

አይተውት ፡

ፏኛ ተመልክተውት ፤
ፔኛ ሊተውት አይገባም ።

ሻንቆ ፡

ፏኛ ጥቁር ፤
ፔኛ ቪሕን አንቆ ።

ሠራን ፡

ፏኛ ፈጠረን ፡ አደረገን ፤
ፔኛ አመድማ ።

ፋንታዬ ፡

ፏኛ የኔ ፋንታ (ድርሻዬ)
ፔኛ የሰው ስም ።

ክፍል ፬ ፡

የፊደላት ወይም የቃላት ቅኔ አፈታት ፤

የፊደላት ወይም የቃላት ቅኔ አፈታት የተባለው ፡ ሰሙ ለሶው ወይም ለሌላ ነገር ሆኖ እየተነገረ ይጻፍና ወርቁ ደግሞ ለፊደላት ወይም ለቃላት ብቻ ሆኖ እየ ተጻፈ የሚነገርበት ዕውቀት ነው ።

ለምሳሌ ፡

ሰም ፡	ወርቅ ፡
ሰውየው ፡ አንቱ አለው ።	ሰውየው አን ፡ ቱ፡ አለው ።
እሳቱ ገሞራ ሆነ ።	እ ፡ ሳቱ ፡ ገ ፡ ሞ ራ ሆነ ።
ሣሩን ረገጠው ።	ሣ ፡ ሩን ፡ ረገጠው ።
ይህን ያስከትላል ።	ይ ፡ ህን ፡ ያስካትላል ።
አጥንታቸው ነው ።	አ ፡ ጥንታቸው ፡ ነው ።
ላም ፡ በብዙ ትጠቅማለች	ላ ፡ ደግሞ በብዙ ትጠቅ ማለች ።
ዓሣን ፡ ይወዳል ።	ዓ ፡ ሣን ፡ ይወዳል ።
ሞትን ፡ አይፈራም ።	ሞ ፡ ትን ፡ አይፈራም ።
ደሙን ፡ አንጠበጠበ ።	ደ ፡ ሙን ፡ አን ፡ ጠበጠበ ።
አንቺን ፡ አልችልም ።	አን ፡ ቺን ፡ አልችልም ።
ለማ ፡ መጀመሪያ ነው ።	ለማ ! መጀመሪያ ነው ።

ሰም ፡	ወርቅ ፡
ቃሉን ፡ ያከብራል ።	ቃ ፡ ሉን ፡ ያከብራል ።
ጠጅ ፡ አማረው ።	ጠ ፡ ጅ ፡ አማረው ።
ብቅል ፡ አይደለም ።	ብ ፡ ቅል ፡ አይደለም ።
ገጠሬ ነው ።	ገ ፡ ጠሬ ፡ ነው ።
ገንቦ ፡ ተሸክሞአል ።	ገን ፡ ቦ ፡ ተሸክሞአል ።
እነዚያ ሰዎች በተራ ይጻ ፋሉ ።	እነዚያ ፡ ሰ ፡ ዎ ፡ ች ፡በተራ ይጻፋሉ ።
ዋንዛን ፡ ይለቅማል ።	ዋን ፡ ዛን ፡ ይለቅማል ።
እንደገና ፡ አሁን መጣ ።	እንደ ፡ ገና ፡ አሁን መጣ ።
እንደገና ፡ አሁን መጣ ።	እንደገ ፡ ና ፡ አሁን መጣ ።
አደጋ ፡ አይደለም ።	አ ፡ ደጋ ፡ አይደለም ።
አደጋ ፡ አይደለም	አ ፡ ደ ፡ ዘንድ አይደለም
የተከፋ ፡ ተደፋ ።	የ ፡ ተከፋና ተደፋ
ጣሰው ፡ አይደለም ።	ጣ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።
ከሮጠ ፡ የቀደመ ።	ከ ፡ ሮጠ ። የ ፡ ቀደመ ።
ሰውን ፡ ይቀድማል ።	ሰ ፡ ውን ፡ ይቀድማል ።
ጐተሪ ውን ይጠብቃል ።	ጐ ፡ ተራውን፡ ይጠብቃል ።
ሲበላ ፡ ይስቃል አሉ ።	ሲ ፡ በላ ላይ ፤ ይስቃል አሉ ።
አበበ ፡ ሲያወራ ተሰማ ።	አ ፡ በበ ፡ ላይ ፡ ሲያወራ ፡ ተሰማ ።

ሰም ፤	ወርቅ ፤
ሣጥን ይገዛል ።	ሣ ፡ ጥን ፡ ይገዛል ።
ቲሳሳቁ ።	ቲ ፡ ሳ ፡ ሳቁ ።
አቦዘኔ ተሠራ ይባላል ።	አ፡ቦዘኔ። ተ፡ሠራ፡ይባላል።
ተፈሪ ነው ።	ቲ ፡ ፈሪ ፡ ነው ።
ባለ ልጅ ያስባል ።	ባ ፡ ለልጅ ፡ ያስባል ።
ጠበቃ መጣ ።	ጠ ፡ በቃ ፡ በኩል መጣ።
ጥሩ ጨዋታ ነው ።	ጥሩ ፡ ጨዋ ፡ ታ ፡ ነው ።
በሉ ኺዱ ።	በሉ ፡ በኩል ኺዱ ።
፩ኛ ሀገር ነው ።	፩ኛ ሀ ፡ ገር ፡ ነው ።
አቶላ ኾነ ።	አ ፡ ቶላ ፡ ጋር ሆነ ።
ወጡን አመጣው ።	ወ ፡ ጡን ፡ አመጣው ።
ቄስ አቶ አይባሉም ።	ቄ ፡ ስ ፡ አ ፡ ቶ ፡ አይባሉም
ሙላቱ ነው ።	ሙ ፡ ላቱ ፡ ነው ።
ጣመን ያዘው ።	ጣ ፡ መን ፡ ያዘው ።
ስብቅ ብሏል ።	ስ ፡ ብቅ ፡ ብሏል ።
ማጠብን አይወድም ።	ማ ፡ ጠብን ፡ አይወድም ።
ሲጠራቸው ነው ።	ሲ ፡ ጠራቸው ፡ ነው ።
ትለቃለች ።	ት ፡ ለቃለች ።
ሰንከኛ አደረጉት ።	ሰን ፡ ከኛ ፡ አደረጉት ።
ጥጥ ነው ።	ጥ ፡ ጥ ፡ ነው ።

ሰም ፡	ወርቅ ፡
ዓለሙ መጽሐፉን አስረ ከበ ።	ዓ ፡ ለሙ ፡ መጽሐፉን አስ ረከበ ።
የዓ . ነገሩን ቃላት ብትን ትን አረጋቸው ።	የዓ . ነገሩን ፡ ቃላት ፡ ብ ፡ ትንትን ፡ አረጋቸው ።
ከጂ ፡ ራት የለውም ።	ከ ፡ ጂራት ፡ የለውም ።
ጓደኛህ ፡ ስለ ሆነ ፤ ሰውን አትጥላ ።	ጓደኛህ ስለ ሆነ ፤ ሰ ! ውን ፡ አትጥላ ።

ክፍል ፭ ፡

የቅኔ ሐረጎች አቀማመጥን ማስተካከል ፤

፪ ወይም ፫ ሐረጎች ለ፩ ቤት ተሰጥተው የሚገ
ኙበት አንዳንድ የግጥም ቅኔ ይገኛል ። እንደዚህ ያለ
ውም ቅኔ ሲያጋጥም በወል ግጥም ደንብ ለመዝፈን
እንዲመች ፪ኛውን ሐረግ ለይቶ ከመጀመሪያው
ሐረግ በታች ማዋል ፡ ፫ኛም ቢኖር ከ፪ኛው ሐረግ
ሥር ማስቀመጥ ነው ። ከዚህም በኋላ ያው አንዱ
ቤት ለመጀመሪያው ፡ ለ፪ኛውና ለ፫ኛው ሐረጎች
በድጋሚ እንዲነገር ማድረግና ፡ የግጥም ቅኔውንም
ባለ ፫ ወይም ባለ ፬ መሥመሮች እንዲሆን አቀማመ
ጡን ማስተካከል ፡ ወይም ማቃናት ይገባል ፤ ምክ
ንያቱም ለ፩ ሰው ፩ ረዥምና ፩ አጭር እግሮች ቢኖ
ሩት ፤ ትክክል እንደማይረግጡለት ሁሉ ፤ እንደዚ
ሁም ፡ ረዥሙና አጭሩ የግጥም መሥመሮች ፡ ለወል
ግጥም ሁሉ ከተወሰኑለት የንባብና የዜማ ሥርዓት
ጋር የማይስማሙ በመሆናቸው ነው ።

ለምሳሌ

ቅኔው ፡ ያቺን ቀጭን ኩታ ፡ ያቺን ጥበብ ኩታ ፡ ሆዴ
እየወደዳት ፤
አላዋቂ ሰፊ ፡ ባላጨማደዳት ።

ሲቃና ፡ ያችን ቀጭን ኩታ ፡ ሆዴ እየወደዳት ፤
ያቺን ጥበብ ኩታ ፡ ሆዴ እየወደዳት ፤
አላዋቂ ሰፊ ፡ ባላጨማደዳት !

ቅኔው ፡ ከሸዋ ከትግሬ ፡ ተጐጃም ተጐንደር ፡ ቀለ
ቤን ብልኽ ፤
ሁል ጊዜ ተከፋ ፡ ለምን ትላለኽ ፡-

ሲቃና ፡ ከሸዋ ከትግሬ ፡ ቀለቤን ብልኽ ፤
ተጐጃም ተጐንደር ፡ ቀለቤን ብልኽ ፤
ሁል ጊዜ ተከፋ ፡ ለምን ትላለኽ ፡-

ቅኔው ፡ ያን ሁሉ ዕውቀትህን ፡ ያን ሁሉ ጥበብህን
የት አደረስኽው ፡-
እረግ አንዱ ጠፋህ ፡ የምትመልሰው !

ሲቃና ፡ ያን ሁሉ ዕውቀትክን ፡ የት አደረስክው ፡-
ያን ሁሉ ጥበብህን ፡ የት አደረስክው ፡-
እረግ አንዱ ጠፋህ ፡ የምትመልሰው !

ቅኔው ፡ ያ ማለፊያ ጸጉርኽ ፡ ያ ማለፊያ ዓይንህ ፡
እንዴት አድሮ ይሆን ፡-

መጥቼ እንዳላይህ ፡ ካልተጠራሁ አይሆን ።
ሲቃና ፡ ያ ማለፊያ ጸጉርህ ፡ እንዴት አድሮ ይሆን ፡-
ያ ማለፊያ ዓይንህ ፡ እንዴት አድሮይሆን ፡-
መጥቼ እንዳላይህ ፤ ካልተጠራሁ አይሆን ።
ቅኔው ፡ የዚያ ማዶ ሰዎች ፡ አያምራቸው ምንጣፍ ፡
አያምራቸው ነት ፤
ያ ማሴን የኛ ነው ፡ ፊት የወሰዱት ።
ሲቃና ፡ የዚያ ማዶ ሰዎች ፡ አያምራቸው ነት ፤
አያምራቸው ምንጣፍ ፡ አያምራቸው ነት ፤
ያ ማሴን የኛ ነው ፡ ፊት የወሰዱት ።
ቅኔው ፡ ኮላሽና ታሞ ፡ አፍቀራንም ጭምር ፡ ባን
ድነት ያማሉ ፤
መቅደላን የንጉሥ ደም ፡ አለበት ይላሉ ።
ሲቃና ፡ ኮላሽና ታሞ ፡ ባንድነት ያማሉ ፤
አፍቀራንም ጭምር ፡ ባንድነት ያማሉ ፤
መቅደላን የንጉሥ ደም ፡ አለበት ይላሉ ።
ቅኔው ፡ ክብርዎ ትልቅ ነው ፡ ሀብትዎ ብዙ ነው ፡
ችግር የለብዎ ፤
ማዘን መነገድን ፡ ማን አስተማረዎ ፡-
ሲቃና ፡ ክብርዎ ትልቅ ነው ፡ ችግር የለብዎ ፤
ሀብትዎ ብዙ ነው ፡ ችግር የለብዎ ፤
ማዘን መነገድን ፡ ማን አስተማረዎ ፡-

ቅኔው ፡ ከሰማይ ዝቅ አርጎ ፡ ከምድር ከፍ አርጎ
አሠርቶ ቤቱን ፤
በመስኮት አግብቶ ፡ ይሞቃል ጣዪቱን ።
ሲቃና ፡ ከሰማይ ዝቅ አርጎ ፡ አሠርቶ ቤቱን ፤
ከምድር ከፍ አርጎ ፡ አሠርቶ ቤቱን ፤
በመስኮት አግብቶ ፡ ይሞቃል ጣዪቱን ።
ቅኔው ፡ እናቴ ቤት ኼጄ ፡ የመጣሁበትን ፡
ገና ሳልናገር ፤
በሆድህ ምን አለ ፡- ብላ ትለኝ ነበር ።
ሲቃና ፡ እናቴ ቤት ሄጄ ፡ ገና ሳልናገር ፤
የመጣሁበትን ፡ ገና ሳልናገር ፤
በሆድህ ምን አለ ፡- ብላ ትለኝ ነበር ።
ቅኔው ፡ ካባ አትበዪኝ እንጂ ፡ ልብስ አትበዪኝ
እንጂ ፡ ትግልስ ዐውቃለሁ ፤
አሁን ያቺን ጥዬ ፡ ወዳንቺ እመጣለሁ ።
ሲቃና ፡ ካባ አትበዪኝ እንጂ ፡ ትግልስ አውቃለሁ ፤
ልብስ አትበዪኝ እንጂ ፡ ትግልስ ዐውቃለሁ ፤
አሁን ያቺን ጥዬ ፡ ወዳንቺ እመጣለሁ ።
ቅኔው ፡ ማዱ ሳይነሣ ፡ ኺዱ ሳይሏችሁ ፡ ስለ ምን
መጣችሁ ፡-
ስብሐት ለአብ ቢቀር ፡ ደግ ነው ብላችሁ ፡-

ሲቃና ፡ ማዱ ሳይነግ ፡ ስለ ምን መጣችሁ ፡-
ኸዱ ሳይሏችሁ ፡ ስለ ምን መጣችሁ ፡-
ስብሐት ለአብ ቢቀር ፡ ደግ ነው ብላችሁ ፡-

ቅኔው ፡ ለካስ ቄስ በሬ ነው ! እየጠጣ ውሃ ፡ እየ
በላ ሣር ፤
ሲሞት ፈትቶት ኼደ ! ያን ሁሉ አገር !
ሲቃና ፡ ለካስ ቄስ በሬ ነው ! እየበላ ሣር ፤
እየጠጣ ውሃ ፡ እየበላ ሣር ፤
ሲሞት ፈትቶት ኼደ ፤ ያን ሁሉ አገር ።

ቅኔው ፡ እኔ ወፍራም ቀሚስ ፡ እኔ ወፍራም ኩታ ፡
ለብሻለሁ ብዬ ፤
በዚህም በዚህም ፡ አከላቴ ታዬ !
ሲቃና ፡ እኔ ወፍራም ቀሚስ ፡ ለብሻለሁ ብዬ ፤
እኔ ወፍራም ኩታ ፡ ለብሻለሁ ብዬ ፤
በዚህም በዚህም ፡ አካላቴ ታዬ !

ቅኔው ፡ ሽማ ግዛ ብዬ ፡ ቀሚስ ግዛ ብዬ ፡ ሰድጂው
ነበረ ፤
አያ ወልደ ኪዳን ፡ ገበያ ባልቀረ !
ሲቃና ፡ ሽማ ግዛ ብዬ ፡ ሰድጂው ነበረ ፤
ቀሚስ ግዛ ብዬ ፡ ሰድጂው ነበረ ፤
አያ ወልደ ኪዳን ፡ ገበያ ባልቀረ !

ቅኔው ፡ ምነዋ ጐጃሜ ፡ ባሌን ጥሎ መጣ ፡ ትለኛ
ለህ አሉ ፡-
ምን ትዋብ አዳልን ፡ ምነው እኔ ሁሉ ፡-
ሲቃና ፡ ምነዋ ጐጃሜ ፡ ትለኛለህ አሉ ፡-
ባሌን ጥሎ መጣ ፡ ትለኛለህ አሉ ፡-
ምን ትዋብ አዳልን ፡ ምነው እኔ ሁሉ ፡-

ቅኔው ፡ ባልሽ ወዴት ኼደ ፡- ብለን ብንጠይቃት ፡
ስለ ጉዳያችን ፤
ተሰብሮ አሁን መጥቶ ፡ ተኝቷል አለችኝ ።
ሲቃና ፡ ባልሽ ወዴት ኼደ ፡- ስለ ጉዳያችን ፤
ብለን ብንጠይቃት ፡ ስለ ጉዳያችን ፤
ተሰብሮ አሁን መጥቶ ፡ ተኝቷል አለችን ።

ቅኔው ፡ ባባ ፈንዘ ጠምሩ ፡ በመንገሻ ጠምሩ ፡ ወትሮ
የጐዳኝ ፡
ተመልሶ መጥቶ ፡ መግቢያ አሳጣኝ ።
ሲቃና ፡ ባባ ፈንዘ ጠምሩ ፡ ወትሮ የጐዳኝ ፤
በመንገሻ ጠምሩ ፡ ወትሮ የጐዳኝ ፤
ተመልሶ መጥቶ ፡ መግቢያ አሳጣኝ ።

ቅኔው ፡ ታላቅና ታናሽ ፡ ሌላም የሚበላ ፡ ሳለ በቤትሽ ፤
አንቺ የሰው ዶሮ ፡ ምን አስፈለገሽ ፡-
ሲቃና ፡ ታላቅና ታናሽ ፡ ሳለ በቤትሽ ፤

ሌላም የሚበላ ፡ ሳለ በቤትሽ ፤
አንቺ የሰው ዶሮ ፡ ምን አስፈለገሽ ፡-

ቅኔው ፡ ትናንትና በቀን ፡ ከትናንትም በፊት ፡ ገበያ ነበሩ ፡
ዛሬስ ደጃች ተድላ ፡ የት ጠፉ ካገሩ ፡-

ሲቃና ፡ ትናንትና በቀን ፡ ገበያ ነበሩ ፤
ከትናንትም በፊት ፡ ገበያ ነበሩ ፤
ዛሬስ ደጃች ተድላ ፡ የት ጠፉ ካገሩ ፡-

ቅኔው ፡ ልጄን አትጥሉብኝ ፡ ልጄን አትሙብኝ ፡ ቢአዛችሁ ተሹሞ ፤
አዞ አያውቅምና ፡ ከዚህ አስቀድሞ ።

ሲቃና ፡ ልጄን አትጥሉብኝ ፡ ቢያዛችሁ ተሹሞ ፤
ልጄን አትሙብኝ ፡ ቢያዛችሁ ተሹሞ ፤
አዞ አያውቅምና ከዚህ አስቀድሞ ።

ቅኔው ፡ በሹመት ቢበልጡኝ እንዴት በነደደኝ እንዴት በቆጨኝ !
እኒያም ጭቃ ናቸው ፡ እኔም ጭቃ ነኝ ።

ሲቃና ፡ በሹመት ቢበልጡኝ ፡ እንዴት በቆጨኝ !
እንዴት በነደደኝ ፡ እንዴት በቆጨኝ !
እኒያም ጭቃ ናቸው ፡ እኔም ጭቃ ነኝ ።

ቅኔው ፡ ትንሽ እህል ቅመሽ ፡ ጥቂት ወተት ጠጪ ፡
ላንቺም ይሻልሻል ፤
ባልሽ አልቦ ይዞ ፡ ያስፈርድብሻል ።

ሲቃና ፡ ትንሽ እህል ቅመሽ ላንቺም ይሻልሻል ፤
ጥቂት ወተት ጠጪ ፡ ላንቺም ይሻልሻል ፤
ባልሽ አልቦ ይዞ ፡ ያስፈርድብሻል ።

ቅኔው ፡ ኢየሱስ ናዝራዊ ፡ ለካ በጉተና ፡ ተከፍክፎ ኖሮ ፤
ይሽው ባንተ ጊዜ ፡ ተሠራ ዘንድሮ ።

ሲቃና ፡ ኢየሱስ ናዝራዊ ፡ ተከፍክፎ ኖሮ ፤
ለካ በጉተና ፡ ተከፍክፎ ኖሮ ፤
ይሽው ባንተ ጊዜ ተሠራ ዘንድሮ ።

ቅኔው ፡ ይቆርጡኝም እንደሁ ፡ ይገድሉኝም እንደሁ ፡
ይሽው ቆምኩልዎ
ያለም ጣም ምኒልክ ብዬ ሰደብኩዎ ።

ሲቃና ፡ ይቆርጡኝም እንደሁ ፡ ይሽው ቆምኩልዎ ፤
ይገድሉኝም እንደሁ ፡ ይሽው ቆምኩልዎ ፤
ያ ለምጣም ምኒልክ ፡ ብዬ ሰደብኩዎ ።

ቅኔው ፡ ከናትም ካባትም ፡ ከትም ከወንድምም ፡ የባል ሞት ይብሳል ፤
እንደ ቁራ አሞራ ፡ ደርሶ ቤት ያፈርሳል ።

ሲቃና ፡ ከናትም ካባትም ፡ የባል ሞት ይብሳል ፤

ከትም ከወንድምም ፡ የባል ሞት ይብሳል ፤
እንደ ቁራ አሞራ ፡ ደርሶ ቤት ያፈርሳል ።

ቅኔው ፡ ጐጃምስ ምን አለ ፡- ዳሞትስ ምን አለ ፡- ይሽ
ንን ሲሰማ ፤
የጁ ተለቀሰ የበለው ፡ ተሰማ ።

ሲቃና ፡ ጐጃምስ ምን አለ ፡- ይሽንን ሲሰማ ፤
ዳሞትስ ምን አለ ፡- ይሽንን ሲሰማ ፤
የጁ ተለቀሰ ፡ የበለው ተሰማ ።

ቅኔው ፡ ቀሚሴንም ሰጠሁ ፡ ድርቤንም ሰጠሁ ፡ አለቀ
ስለቱ ፤
ለመርጡለ ማርያም ፡ ለዚያች ለደብሪቱ ።

ሲቃና ፡ ቀሚሴንም ሰጠሁ ፡ አለቀ ስለቱ ፤
ድርቤንም ሰጠሁ ፡ አለቀ ስለቱ ፤
ለመርጡለ ማርያም ፡ ለዚያች ለደብሪቱ ።

ቅኔው ፡ ይጎደጎና አብርሃ ፡ ከትግሬ ተነሥተው ፡
ወደ ጐጃም ሲያልፉ ፤
ተመቻቸውና ፡ ይፋግ አራገፉ ።

ሲቃና ፡ ይጎደጎና አብርሃ ፡ ወደ ጐጃም ሲያልፉ ፤
ከትግሬ ተነሥተው ፡ ወደ ጐጃም ሲያልፉ ፤
ተመቻቸውና ፡ ይፋግ አራገፉ ።

ቅኔው ፡ በስተወሌም በኩል ፡ በስተጉግሣም በኩል ፡
በስታመዴ በኩል ፡ ሳሳብኝ ሌማቱ ፤
ጠፍታለች መሰለኝ ፡ እንጀራ ጣዪቱ ።

ሲቃና ፡ በስተወሌም በኩል ፡ ሳሳብኝ ሌማቱ ፤
በስተ ጉግሣም በኩል ፡ ሳሳብኝ ሌማቱ ፤
በስታመዴም በኩል ፡ ሳሳብኝ ሌማቱ ፤
ጠፍታለች መሰለኝ ፡ እንጀራ ጣዪቱ ።

ቅኔው ፡ ሐምሌ ድንጋይ ይዟል ፡ ናሴ ሰይፍ መዟል ፡
መስከረም ጦር ይዟል ፡ ሰው ሊገድሉላችሁ ፤
አትገላግሉም ወይ ፡- ያላችሁ ያላችሁ ።
ሲቃና ሐምሌ ድንጋይ ይዟል ፡ ሰው ሊገድሉላችሁ ፤
ናሴ ሰይፍ መዟል ፡- ሰው ሊገድሉላችሁ ፤
መስከረም ጦር ይዟል ፡ ሰው ሊገድሉላችሁ ፤
አትገላግሉም ወይ ፡- ያላችሁ ያላችሁ ።

ቅኔው ፡ የዣጋ ወይዘሮ ፡ የስናን ወይዘሮ ፡ ያስቀም
ጧል እንጂ ፡ ቅልን ተጠንቅቆ ፤
ደረቁን በላነው ፡ ያ ሁሉ ጨው አልቆ ።
ሲቃና ፡ የዣጋ ወይዘሮ ፡ ቅልን ተጠንቅቆ ፤
የስናን ወይዘሮ ፡ ቅልን ተጠንቅቆ ፤
ያስቀምጧል እንጂ ፡ ቅልን ተጠንቅቆ
ደረቁን በላነው ፡ ያ ሁሉ ጨው አልቆ ።

ቅኔው ፡ የኛ ቤተሰቦች ፡ አባባ ኼደዋል ፡ እዬዬ !
ብላችሁ ፡ ዋይ በሉና አልቅሱ ፤
እንግዲህ ዕወቁት ፡ እንዳይመለሱ ።

ሲቃና ፡ የኛ ቤተሰቦች ፡ ዋይ ! በሉና አልቅሱ ፤
አባባ ኼደዋል ፡ ዋይ ! በሉና አልቅሱ ፤
እዬዬ ! ብላችሁ ፡ ዋይ በሉና አልቅሱ ፤
እንግዲህ ዕወቁት ፡ እንዳይመለሱ ።

እንዲሁም በጣም ጥቂቶች የሆኑ ቅኔዎች በሐረጎች ብዛት በኩል ልክ የነዚህ ዓይነት ጠባይ ያላቸው ሲሆኑ ፤ ለማቃናት ግን በድጋሚ እየገባ የሚነገረው ፤ የመጀመሪያው ሐረጋቸው ብቻ ነው ። በዚህም ጊዜ በግጥሙ ፡ ፪ኛው ሐረግ የነበረው በተቃናው ላይ ለፈተኛው መሥመር ቤት ይሆንና እንዲሁም በግጥሙ ለፈተኛው መሥመር ቤት የነበረው በማቃኛው ላይ ለ፪ኛው መሥመር ቤት ይሆናል ።

ለምሳሌ

ቅኔው ፡ የናቴ አገር ገረን ፡ እንሳሮ ያባቴ ፡ የኔ መርሐ - ቤቴ ፤
ዝማ ተጣጥቤ ፡ ልገባ ነው ቤቴ ።
ሲቃና ፡ የናቴ አገር ገረን ፡ እንሳሮ ያባቴ ፤

የናቴ አገር ገረን ፡ የኔ መርሐ - ቤቴ ፤
ዝማ ተጣጥቤ ፡ ልገባ ነው ቤቴ ።
ቅኔው ፡ እምዬ ምኒልክ ! ጃኖ አልለምንህም ፡ በቅሎ አልለምንህም ፤
ዓምና ነበር እንጂ ፡ ዘንድሮስ የለህም ።
ሲቃና ፡ እምዬ ምኒልክ ! ጃኖ አልለምንህም ፤
እምዬ ምኒልክ ! በቅሎ አልለምንህም ፤
አምና ነበር እንጂ ፡ ዘንድሮስ የለህም ።

ማስገንዘቢያ ፡

ከዚህ በላይ በተገለጸው ዘዴ ሊያቃኑትና ሊያስተካክሉት የማይቻል የግጥም ቅኔ ይገኛል ። ይኸውም ለርሱ የሚሆን ዘፈን የማይገኝለት ስለሆነ ፡ ፍጹም የቅኔ ጸያፍ ነው ፤ ዳሩ ግን ቍጥሩ እጅግ በጣም ያነሰ ነው ።

ለምሳሌ ፡

መንኩስ ይለኛል ሰው ሁሉ ፡ ብመነኩስ ምን አለ ፡-
አብሮ የኖረ ሆነና ፡ አመልኳሹ እንቢ አለ ።
እነሆ ! ከዚህ በላይ ለምሳሌ የተጻፈው ቅኔ ሐሳብን ለመግለጽ ያህል የተቀኘ ነው እንጂ ፤ ዓይነቱ ከመዲና ግጥም ፡ ወይም ከወል ግጥም ቅኔዎች አይደለምና ይህን የመሰለ የግጥም ቅኔ ሁሉ ከዚህ ቀደም ለታወቁት ዘፈኖች የማይስማማ ፍጹም የቅኔ ጸያፍ ነው ።